''እርሱ ግን በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ፤ ስለ እኛም ታመመ፤ እኛም እንደ ታመመ፥ እንደ ተገረፈም ቆጠርነው። እርሱ ግን ስለ ኃጢአታችን ቆሰለ፤ ስለ በደላችንም ታመመ፤ የሰላማችንም ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበረ፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።''

ት/ኢሳ ፶፫፥፬-፭

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች

፬ መልእክት

፮ ሪፖርታዥ

፱ ቤተ አብርሃም

፲፪ ቃለ መጠይቅ

፲፮ የሕፃናት ዓምድ

፲፱ ትዝብት

፳፩ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ


☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል

newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ

ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር

ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር

ረቂቅ መቻል

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር

ግደይ ገብሬ

ጸሐፊ

ገነት ታደሰ

# ማኅበረ ቅዱሳን የስድስት ወር የሥራ አመራር ጠቅላላ ጉባኤውን አካሄደ

*በጋዜጣው ሪፖርተር*



*አቶ ተስፋዬ ቢሆነኝ*
*የማኅበረ ቅዱሳን ዋና ሰብሳቢ*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን የስድስት ወር የሥራ አመራር ጉባኤውን ከሚያዝያ ፩ እስከ ሚያዝያ ፫ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም አካሄደ።

ለሦስት ተከታታይ ቀናት በተካሄደው በዚሁ ጉባኤ ላይ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር የተወከሉ የማዕከላት አባላት እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች የተገኙተዋል። በጉባኤውም የሥራ አስፈጻሚ ጽ/ቤት የሥራ አስፈጻሚ ጉባኤ፣ የኤዲቶሪያል ቦርድ ማስተባበሪያ፣ የኦዲት አገልግሎት ሪፖርታቸውን ያቀረቡ ሲሆን የስድስት ወር የሥራ አመራር ቃለ ጉባኤም ጸድቋል።

በቀጣይ ቀናትም የቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ አገልግሎት ተግዳሮትና ቀጣይ አቅጣጫዎች፣ ስልታዊ ዕቅድ ማሻሻያ፣ የተቋማዊ ለውጥ መነሻ ሐሳቦች እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፖሊሲ መነሻ ሐሳብ የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ተነሥተው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

ማኅበሩ ስልታዊ ዕቅድ ከጀመረ አራተኛ ዓመት ላይ እንደሚገኝ የገለጹት የማኅበሩ ዋና ጸሐፊ አቶ ውብሸት ኦቶሮ የስልታዊ ዕቅዱ አጠቃላይ ይዘት ስድስት ወሳኝ ጉዳዮችን፣ ፳፱ ግቦችን ፪፻፳፫ ስልቶችና አመላካቾች የተካተቱበት እደሆነ፤ የስልታዊ ዕቅዱ ዋና እሳቤም ከአጋር እና ከተባባሪ አካላት ጋር በጋራ እንደሚሠራ እንዲሁም የሰው ኃይል ልማት ላይ እንደሚያተኩርም ገልጸዋል።

በጉባኤው መዝጊያም የማኅበሩ ዋና ሰብሳቢ አቶ ተስፋዬ ቢሆነኝ በሀገራችን በኢትዮጵያ ያለውን ወቅታዊ ሁኔታን አስመልክተው ችግሩ እጅግ እየተወሳሰበ መምጣቱን ገልጸዋል። አክለውም የማኅበሩ አባላት ከወትሮ በተለየ መልኩ ሱባኤ ገብተው ጸሎት በማድረግ እንዲሁም በማስተማር እና በመምከር ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።



# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ለሩሲያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ የምስጋና ደብዳቤ ላኩ

*በጋዜጣው ሪፖርተር*

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳስ ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ሃይማኖትን መሠረት የደረጉ ጥቃቶች ለደረሰባቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ላደረጉት ጸሎት እና ድጋፍ ለሩሲያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ክሪል ሚያዚያ ፫ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም የምስጋና ደብዳቤ መላካቸውን ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ ዘግቧል።

ቅዱስነታቸው የምስጋና ደብዳቤውን የላኩት የሞስኮና የመላው ሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የሆኑት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ክሪል በኦሮምያ ክልል ምሥራቅ ወለጋ ዞን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስቲያን ምእመናን መገደላቸውን አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ የኀዘን መግለጫ እንዲሁም የጥቃቱ ሰለባ ለሆኑ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ድጋፍ እንደሚያደርጉ የሚገልጽ ደብዳቤ መላካቸውን ተከትሎ ነው።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ በሀገሪቱ ውስጥ እየተካሄዱ ያሉት ጥቃቶች በዋነኝነት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ እና መንፈሳዊ ተቋማት ላይ ያነጣጠሩ መሆናቸውን በምስጋና ደብዳቤያቸው ላይ አክለው ገልጸዋል።

የሞስኮና የመላው የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ክሪል በየካቲት ወር ፳፻፲፫ ዓ.ም ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ የኀዘን መግለጫ ደብዳቤ መላካቸውን አስመልክቶ መዘገባችን ይታወሳል።

# የማኅበረ ቅዱሳን መደበኛ አገልጋዮች የመቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከልን ጎበኙ

**. *ከቁሳዊ ድጋፍ በተጨማሪ መንፈሳዊ ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ተገለጸ***



አቶ ግሩም አሥራት

*በጋዜጣው ሪፖርተር*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ማደራጃ መምሪያ የማኅበረ ቅዱሳን መደበኛ አገልጋዮች ሚያዚያ ፩ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም መቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከልን በመጎብኘት የመቀሪቢያ አልባሳትንና የጸሎት መጻሕፍትን ለገሱ።

የጉብኝት ጉዞው አስተባባሪ የሆኑት አቶ ግሩም አሥራት ‹‹የታመሙትን መጠየቅ፣ የተቸገሩትንም መርዳት ግዴታችን ነውና ለአረጋውያኑና ለአእምሮ ሕሙማኑ ከቁሳዊ ድጋፍ ባሻገር መንፈሳዊ ድጋፍ ልናደርግላቸውው ይገባል›› ብለዋል። አስተባባሪው አክለውም ‹‹በቃል የምናስተምረውን በተግባር ማሳየት ይጠበቅብናል›› ሲሉ ተናግረዋል። በቀጣይም የቀሩትን የማኅበረ ቅዱሳንን አባላት በማሳተፍ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል።

በማዕከሉ የተገኙት የማኅበሩ መደበኛ አገልጋይ ቀሲስ ይግዛው መኮንን በበኩላቸው ‹‹መስማት ማየትን አይተካውም የምንሰማውና የምናየው የተለያየ ነው ፤ እኔ እስከዛሬ ስለ ማዕከሉ ሳልሰማ ቀርቼ አይደለም ፤ ነገር ግን በፊት ከነበረኝ አመለካከት ዛሬ ብዙ ነገር ተምሬአለሁ ፤ መማር ብቻ ሳይሆን ብዙ ነገር ለማድረግ ወስኛለሁ፤ ስዚህ ሌሎቻችንም በአካል መጥተን ማዕከሉን አልናይ ይገባል።›› ብለዋል።

አረጋውያኑም የማኅበሩ አገልጋዮች ማዕከሉ ድረስ በመሄድ ስላደረጉላቸው ድጋፍ ልባዊ ምስጋናቸውን ያቀረቡ ሲሆን የማዕከሉ መሥራች ክቡር ዶክተር ብንያም በለጠም ‹‹አረጋውያኑን እና የአእምሮ ሕሙማኑን ስለጠየቃችኋቸው፣ ድጋፍም ስላደረጋችሁላቸው ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ›› ያሉ ሲሆን በመቀጠልም ‹‹የቤተ ክርስቲያን አባቶች መጥተው እንዲረዱን እንዲሁም ፹፩ ፰፩ ላይ OK ብለው በእጅ ስልካቸው ላይ በመላክ እና አንድ ብር በመስጠት ጎዳና ላይ የወደቁ ወገኖቻችንን እናንሳ ዘንድ በእናንተ በኩል አስፈላጊውን ትብብር እንድታደርጉል›› ሲሉ መልእክታቸውን አስተላለፈዋል።



ቀሲስ ይግዛው መኮንን

# «ዘግይተናል፤ እንዳንቀር ግን እንጠንቀቅ!»

በረጅም ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሀገር እድገት ያበረከተችው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ለሀገር ያላት አስተዋጽኦ የሚነሣው ምእመናን እንደ ሀገር ዜጋ ከሚኖራቸው ታማኝነትና ባለ አደራነት ነው። ይህም የሚሆነው ከሀገር መሪዎችና ባለ ሥልጣናት ጀምሮ እስከ ተርታው ኗሪ ድረስ እንደ ባለ ሀገር በማሰብ ስለሚኖሩ ነው። ሌላው ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ያላትን የማኅበራዊ አገልግሎት ድርሻ መሠረት ያደረገ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች፤ ትመክራለች፤ በግብረገብ ታንጻለች፤ ለበጎ አድራጎት እንዲነሣሡ ዜጎችን ታነቃቃለች፤ ለሥራ እንዳይለግሙ ታተጋለች፤ ለነጻነትና ፍትሕ እንዲቆሙ ታጠነክራለች፤ የጥበብ ምንጭ ትሆናለች፤ ምእመናን በመንግሥት የሥራ ዘርፎች ሁሉ ታማኝ ሆነው እንዲያገለግሉ ታሳስባለች፤ ሌሎችም ተዘርዝረው የማያልቁ አስተዋጽኦዎችን በማድረግ ኢትዮጵያ ሀገር ሆና የቆመችበትን ሁኔታ ፈጥራለች። ዛሬም ሆነ ወደፊት ልጆችዋን አሳልፋ ለሀገራዊ ህልውናዋ ትሠራለች።

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሀገርን ችግር ሁሉ ተሸክማ ኢትዮጵያን ብዙ ዘመን አሻግራለች። በሀገር የሚመጣን መከራ ሁሉ በግንባር ቀደምትነት የመከራ ተካፋይ ስትሆን ኖራለች። በዚህም ለልጆቿ መጠለያ ከለላ በመሆን ዘመናትን አሳልፋለች። ስለልጆቿም ራሷን አሳልፋ ሰጥታለች። ይህ መከራም ትናንት ብቻ ሳይሆን ዛሬም የሚሆንባት ነገም የሚከተላት ነው። ለዚህ ምስክሩ ደግሞ የዛሬው ትውልድ በገጠመው ፈተና ውስጥም የመከራውን ሁሉ ቀንበር ተሸካሚ ሆና መገኘቷ ነው።

አሁንም ኢትዮጵያ በጭንቅ ውስጥ ያለች ሀገር ሆናለች። ኢትዮጵያ በእርስ በእርስ ግጭት፣ በውጪ ኃይሎች ወረራ እና በሌሎችም ውስብስብ ችግሮች ተተብትባለች። ሰይጣን ኢትዮጵያን ባለ በሌለ ኃይሉ የከበባት ይመስላል። ዘረኝነት፣ ጭካኔ፣ ድንቁርና ዜጎችን እያጠቁ ነው።

ይህ ሁሉ ቢሆንም ግን ቤተ ክርስቲያን ዛሬም የድርሻዋን በመወጣት ኢትዮጵያን የመታደግ ኃላፊነት አለባት። ቤተ ክርስቲያን ከአስተምህሮዋ የሚመነጭና ከዚች ሀገር ፖለቲካ ጋር የማይጋጭ የፖለቲካ መነጽርን በግልጽ ማበጀት አለባት። ከዚህ እይታ የሚመነጭ ትምህርት፣ ምክርና ተግሣጽ መስጠትም ሁልጊዜ የሚጠበቅባት ጉዳይ ነው። ይህም ትምህርት ምክርና ተግሣጽ ለሰው ሁሉ ኅሊና የሚስማማ ሆኖ በሚዲያዎች መስተጋባት ይኖርበታል። ለዚህ የሚከፈል ዋጋ ካለም ለመክፈል ቆራጥ ርምጃ መውሰድ አለባት።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በኦርቶዶክሳዊነት መነጽሯ በምትሰጠው ትምህርትና ምክር በቅድሚያ የራሷን ልጆች በአንድ ቤት ማሳደር/አንድ ማድረግ/ አለባት። ከዚያም በዘር ሐረግ፣ በቋንቋ፣ በባህል ልዩ ልዩ የሆነውን የውስጧን ኦርቶዶክሳዊ ማኅበረሰብ በኦርቶዶክሳዊ እምነት መነጽር የሀገሩን ፖለቲካ እንዲመለከት በዚያም እንዲግባባና ሀገሩን ከጥፋት እንዲታደግ መሥራት አለባት። ይህ ስለሀገር የምታደርገው ጥረቷ ደግሞ እውን እንዲሆን በኢትዮጵያ የነበረው አንድነትና የእርስ በርስ ማኅበራዊ ትስስርም እንደገና ተመልሶ እንዲጠናከር በመላው ሀገራችን ያሉ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ድምጽ በመስማት በአንድ መቆም አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ የእምነት ቤት መሆኗን ለዓለሙ ማሳየት የምትችለው በዚህ በዘር ለመባላት ባኮበኮበ ትውልድ መካከል ገላጋይና አስታራቂ ሆና መገለጥ ስትችል ነው። ትናንት የነበራትን ክብርም ማስቀጥል የምትችለው በዚህ ደረጃ ስትሠራ ነው።

የአሁኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኦርቶዶክሳዊ

ትውልድ ግን ይህንን ለማድረግ የዘገየ ይመስላል፡፡ ይህ ደግሞ ከፍተኛ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል፡፡ ሌሎች ይህን በሀገር እየዘነበ ካለ የመከራ ዶፍ አስጠላይ ሆነው ለመታየትና በቀጣዩ የኢትዮጵያ ትውልድ ውስጥ ባለውለታና ክፉ ዘመን አሻጋሪ ሆኖ ለመቅረብ መውተርተራቸው ከአሁኑ የቤተ ክርስቲያን ትውልድ መዘግየት የመነጨ ነው፡፡ እውነተኛ ሰላም፣ ግብዝነትም ለሌለበት ፍቅር ምንጩ የሆነች ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የያዘ ትውልድ ኢትዮጵያ ብዙ ሳትጎዳ ጎዘኗም ከልክ ሳያልፍ መፍጠን አለበት፡፡

ለዚህም ደግሞ ወጣቱ ትውልድ መጀመሪያ በሃይማኖት አባቶቹ ላይ የሚያደርሰውን የማይገባ ነቀፌታ እንዲተው የሃይማኖት መሪዎቻችን ሞራል ማደግ ይገባዋል፡፡ ትውልዱ መሪዎቹን ብዙ ጊዜ ታዝቧል፡፡ ከመታዘብ ባለፈ አቅም ቢስ አድርጎ ሥሏቸዋል፡፡ በቅድሚያ ከጥንት ዘመን ጀምሮ የነበረው የሃይማኖት አባቶች ክብር ይመለስ ዘንድ ቤተ ክርስቲያን የመሪዎቿንና አገልጋዮቿን ክብር ለማስለመስ በትጋት መሥራት ይኖርባታል፡፡ በዚህም መሠረት አባቶቻችን የጥንቱን በሚመስል ግብር በልጆቻቸው ዘንድ ከልብ ሊታዩ ከተጣሉአቸውም ሁሉ ከልብ ሊታረቁ ፣ በውስጣቸው ያለውን የዘር፣ የባህል፣ የቋንቋ፣ የጎጥ፣ የጥቅም ግጭትም ወዘተ እርም አድርገው ከውስጣቸው ሊያስወግዱ ይገባል፡፡ ብፁዓን አባቶች የሚደፍሩትን ይቅር መባባል ልጆቻቸው ቀሳውስትና ዲያቆናት ይደፍሩታል፡፡ ከዚያ ደግሞ ምእመናን እርስ በርሳቸው ይቅር ይባባላሉ፡፡ ይህንንም ሁሉ በማየት ትውልድ ሁሉ እርስ በርሱ ይቅር ለማባባል አቅም ያገኛል፡፡ በመጽሐፍ ‹‹ክፉ ከምትሠሩ ይልቅ መልካም ሥራ እየሠራችሁ የእግዚአብሔርንም ፈቃድ እየተከተላችሁ መከራ ብትቀበሉ ይሻላልና፡፡›› (፩ኛ ጴጥ ፫ ፥ ፲፯) ተብሎ እንደተጻፈ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የሚመጣ እስራት፣ ስደት፣ ሞት፣ እንግልት፣ የስም መጥፋት፣ ወዘተ መከራ ቢኖር እንኳን መከራውን መቀበል አስደሳች ይሆናል፡፡

ቅደስት ቤተ ክርስቲያን ከአስተምህሮዋ የሚመነጨውን ይህን መልካም ተግባር በትጋት ለመፈጸም ሀገርን ከሚመሩ የፖለቲካ ኃይሎች ጋር ያለቸልተኝነት በምክክርና በትብብር አብራ ልትሠራ ይገባል፡፡ ከዚያ ያለፈ ነገር ሲመጣ ደግሞ ለምን ብላ ልትጠይቅ ልትገሥጽም ይገባታል፡፡ ከኢትዮጵያ ጥፋት በላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሊያስተክዛት የሚችል ነገር አይኖርምና፡፡ ኢትዮጵያን አስከብራ እንደኖረች ሁሉ በኢትዮጵያ የሚመጣውን መከራ ዛሬም በመቀበል ላይ ናት፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሕዝብን ሁሉ በጥላቻ ከመተያየት ማትረፍ ይጠበቅባታል፡፡ የቤተ ክርስቲያ አምላክ ሀገራችንንና ሕዝቦቿን ከሰይጣን ክፉ ሥራዎች ሁሉ እንዲጠብቃቸው ዘወትር መጸለይ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ግን የቤተ ክርስቲያን ልጆች ዘግይተዋል፡፡ በመሪዎቻችንም ላይ ሰይጣን ከልክ ያለፈ የሚያዘገይ አዚም የጫነባቸው ይመስላል፡፡ ከዚህ አዚም በመውጣት የቤተ ክርስቲያንን መከራ ማቅለል ከመሪዎቿም ከልጆቿም ዘመኑ የሚጠይቀው ጉዳይ ነውና ይህንን ከማድረግ መዘግየት የለብንም፡፡

በቅርብ ዘመን ታሪክ ውስጥ እንኳን በመከራ ውስጥ አልፎ ሀገርና እምነትን ስለማስከበር ምሳሌ የሚሆኑ አባቶች ነበሩ፡፡ በኢትዮጵያ የእነ አቡነ ጴጥሮስ፣ የእነ አቡነ ሚካኤል መልካም ሥራ በእኛም የዘመኑ ኦርቶዶክሳዊ ትውልድ ደም ውስጥ መኖር ይገባዋል፡፡ በግብጽ ጨካኝ እስላማዊ መንግሥት ሥር የወደቀች የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ህልውና ለመጠበቅ ተጋድሎ ሲፈጽሙ የነበሩትን አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊን ማሰብ እና ምን ላይ እንዳለን በግልጽ ያመለክተናል፡፡

ሀገር ከፈረሰ፣ ወገን ከደከመ፣ መላም ከጠፋ በኋላ፣ በስንፍናችንም መባስ ፈጣሪ ቸል ካለን በኋላ ብንነቃ ምን ዋጋ አለው? ዛሬ እንዳናጣው የምንመኘውን ክብርና ጥቅም ሁሉ ብቻችንን ሆነን በምንቀበለው መከራ እናጣዋለን፡፡ ስለዚህ ለመልካም ሥራ ዘግይተናል፤ አሁንም ግን ጊዜ አለ፤ እንዳንቀር እንጠንቀቅ፡፡

# ‹‹መመሪያውን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ማኅበሩና መዋቅሩ ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ››

*- (አቶ ውብሸት ኦቶሮ የማኅበረ ቅዱሳን ዋና ጸሓፊ)*

*በካሣሁን ለምለሙ*

## ክፍል አንድ

መጪው ሀገራዊ ምርጫ ሊካሄድ የአንድ ወር ያህል ጊዜ ብቻ ቀርቶታል፡፡ ምርጫ ቦርድም የጊዜ ሰሌዳ ነድፎ በቅደም ተከተል የሚካሄዱ ፕሮግራሞችን እያካሄደ ይገኛል፡፡ በአንደ ጎኑ በሀገሪቱ ውስጥ የሚታየው ቀውስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቶ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ኢትዮጵያ በአንድ በኩል የእርስ በርስ ግጭትን በሌላ በኩል የምርጫ ፕሮግራምን ተሸክማ ወደፊት ለመራመድ እየሞከረች ያለችበት ሰዓት ላይ ነው ያለነው፡፡

ከአጠቃላይ ሕዝቧ ከግማሽ በላይ የሚሆነው የተዮጵያ ኦርቶዶክስተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመን በመሆነባት ሀገራችን እንደ አንድ ባለመብት ዜጋም ሆነ ከነገው የቅድስት ቤተ ክርስቲያን  ጥቅም አንፃር ኦርቶዶክሳዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የሚወክላትና በፓላማ ስለሚወሰነው ጉዳይዋ  ድምጽ የሚሆናት ተመራጭ ሊኖራት ይገባል፡፡

ይህንንም በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን በየካቲት ፳፻፲፫ ዓ.ም በማኅበረ ቅዱሳን ሥራ አመራር ጉባኤ ጸድቆ የወጣውን መመሪያና በመመሪያው ስለተካተተው የአባላት የፖለቲካ ተሳትፎ፣ መብትና ግዴታዎች እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ የማኅበሩ ዋና ጸሐፊ  አቶ ውብሸት ኦቶሮ ከማኅበረ ቅዱሳን ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቆይታ በምርጫና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ለአባላት፣ እንዲሁም በቅርብ ማኅበሩን ለሚከታተሉ የተለያዩ አካላት በቅርቡ ሰፊ ማብራሪያ  ሰጥተዋል፡፡ ማብራሪያው ሙሉ ሐሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በየካቲት ፳፻፲፫ ዓ.ም በማኅበረ ቅዱሳን ሥራ አመራር ጉባኤ ጸድቆ የወጣውን መመሪያና በመመሪያው ስለተካተተው የአባላት የፖለቲካ ተሳትፎን አስመልክቶ የተሰጠው መስጠት ያስፈለገው በአባላቱ እንዲሁም በውጭ ማኅበሩን በቅርብ በሚያውቁ ሰዎች ዘንድ ብዥታ ስላለ እርሱን ለማጥራት ነው፡፡

በተለይም አባላት በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸው ተሳፎ እና አቋም የተለያየ ቢሆንም  ማኅበሩ ግን በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ እንደተቀመጠው በማንኛውም የፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፤ የትኛውንም ፓርቲ ሆነ ርዕዮተ ዓለም በተለየ መልኩ አይደግፍም፤ እንዲሁም አይቃወምም፤ አባላቱን በተመለከተ ግን እንደ አንድ ዜጋ የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን፣ የመደገፍ፣ አቋም የመያዝ፣ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብቶች ያላቸው ሲሆን ይህንኑ ፍላጎታቸውን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ግን የያዙትን ፖቲካዊ አቋም የማኅበሩ አቋም አድገው መውሰድ ተገቢ አይደለም፡፡ በሌላም በኩል ማኅበሩ በማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ አይሳተፍም ሲባል የማኅበሩ አባል በምንም ዓይነት የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ አይሳተፍም እንዲሁም ጣልቃ መግባት የለበትም የሚል አመለካከት በአንዳንዶች ዘንድ ስላለ እንዲህ ዓይነቱን ብዥታ ለማጥራት ነው በሰነድ ማስቀመጥ እና ማብራራት ያስፈለገው፡፡

በ፲፱፻፺፬ ዓ.ም የወጣው መመሪያ ማኅበሩ በማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ጣልቃ አይገባም፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ለመደገፍ የተሰባሰቡ አባላት የመሠረቱት ነው፡፡ ማኅበሩ መንፈሳዊ ማኅበር እንደመሆኑ መጠን እንደተቋም ከቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ውጪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሠሩትን ሥራ በአጠቃላይ አይሠራም፤

በማኅበሩ መመሪያ ላይ የተቀመጠው አንቀጽም ቢሆን ይህንኑ ሐሳብ ለማጽናት የተቀመጠ አንቀጽ ነው፡፡

ማኅበሩ በፖለቲካዊ ጉዳዮች ጣልቃ አይገባም፤ አይሠራም ሲባል ግን በሌላ መልኩ የሚሠራቸው ሥራዎች የሉትም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ይቃወማል፤ አቋም ይይዛል፤ ምእመናን በቤተ ክርስቲያን እና በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና አቋም እንዲኖራቸውም ይሠራል፡፡ በእርግጥ በመመሪያው አንቀጽ ሁለት ላይ ‹ማኅበሩ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ አይገባም› ማለት ብዙዎች እንደሚያስቡት ቤተ ክርስቲያንን ሊያጠፋ የመጣውን የፖለቲካ ፓርቲ አይቃወምም ማለት አይደለም፡፡ መመሪያው ይህንን በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮዋን፣ ህልውናዋን፣ መብቷንና ጥቅሟን የሚጋፋ የፖለቲካ አቋም ላይ ማኅበሩ መንፈሳዊ ማኅበር እንደመሆኑ መጠን ቤተ ክርስቲያንን መጠበቅ ግዴታ ስላለበት አቋም ይዞ ይሞግታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ማኅበሩ ኦርቶዶክሳውያን ለሀገር የሚጠቅም የቤተ ክርስቲያንን መብት የሚያስጠብቅ ፍትሕ ርትዕን የሚያሰፍን አካል በመምረጥ በሀገራዊ ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይመክራል፡፡ ትላንት ቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰውን በማሰብ ዛሬ ላይ ለምን ብሎ የሚናገርላትን፣ አቋም ይዞ የሚሞግትላትን እንዲሁም ጉዳት ሲደርስባት የሚቃወምላትን አካል አስበው እና ዓላማ አድርገው ይመርጡ ዘንድ ሕገ እግዚአብሔርን በጠበቀ መልኩ በንቃት እንዲሳተፉም ያስተምራል፡፡

ምእመናን በሀገሪቱ ላይ ፍትሕ ርትዕን የሚያሰፍን የፖለቲካ ፓርቲን እንዲመርጡ እና አቋም እንዲይዙ ማኅበሩ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራን ይሠራል፡፡ ይህም ሲባል የትኛውንም የእምነት ተከታይ ለማለት ነው እንጂ ማኅበሩ በተለየ ኦርቶዶክስ ሀገር ይምራ የሚል አቋም የለውም፡፡ የየትኛውም ሃየማኖት ተከታይ ይሁን አለዚያም ሃይማኖት የሌለው ነገር ግን ሀገርን የሚጠቅም እና ሁሉን በእኩል አይቶ የሚያስተዳድር አካልን ምእመኑ እንዲመርጥ ነው ማኅበሩ የሚያበረታታው፡፡ የትኛውም አካል ሀገርን ለመምራት ሥልጣን ላይ ቢወጣ ማኅበሩ ምንም ዓነት ቅራኔ የለውም፡፡ ሀገርን እንደ ሀገር በእኩልነት፣ ለሕዝብ ሰላምን በማምጣት ይምራ እንጂ ማኅበሩ ከዚህ የተለየ አቋምም ሆነ እምነት የለውም፡፡

በመመሪያው አንቀጽ ፫.፫ ላይ እንደተቀመጠው ማኅበሩ ለየትኛውም ርዕዮተ ዓለም፣ ፓርቲ፣ ዕጩና ተመራጭ ይሁንታ አይሠጥም ይላል በሌላው አንቀጽ ፪.፩ ላይ መንግሥት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ልሂቃን እንደ አስፈላጊነቱ የቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን መብት ማስጠበቅን በተመለከተ ያላቸውን አቋም እንዲያሳውቁ፣ እንዲሞግቱ እና እንዲያሚግቱ እንዲጠየቁ ሊያደርግ ይችላል የሚሉት ሁለት ሐሳቦች የሚጋጩ አይደሉም ምክንያቱም የአንቀጹ ትርጓሜ ማኅበሩ እንደ ተቋም የማይፈጽማቸው ጉዳዮች ብሎ በመመሪያው ከጠቀሰው ውስጥ ለየትኛውም ርዕዮተ ዓለም፣የፖለቲካ ፓርቲ፣ ዕጩና ተመራጭ ይሁንታን አይሠጥም የሚል ነው፡፡ ይሁንታ ማለት ይኸኛው የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ያኛው ዕጩ እኛን ይወክለናል፣ ለኦርቶዶክስ የሚበጀው ይሄ ነው ብሎ ዕውቅና አይሰጥም ማለት ነው፡፡ የማኅበሩ ገለልተኝነት አጽንኦት የተሰጠው እና የተሠመረበት ዐቢይ ጉዳይ ነው ሲባልም የማኅበሩ መዋቅር፣ መልካም ስም፣ ሀብት፣ንብረት ለማንኛውም ዓይነት የፖለቲካ ሥራ እንዳይውል ይከለክላል ማለት ነው፡፡ እነዚህም መመሪያዎች ማኅበሩን ከየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ገለልተኛ አድርገው የሚያስጠብቁ ሚዛኖች ናቸው፡፡

ማኅበሩ መንግሥት፣ የፖለቲካ ፓርቲ እና የፖለቲካ ልሂቃን እንደ አስፈላጊነቱ የቤተ ክርስቲያንና የምእመናንን መብትና ጥቅም በተመለከተ ያላቸውን አቋም እንዲያሳውቁ ያደርጋል ማለት ዕውቅና መስጠት አይደለም፡፡ ይልቁንም የፖለቲካ ልሂቃኑም ሆኑ መንግሥት ሐሳባቸውን የሚያሳውቁበት መንገድ ማመቻቸት ነው፡፡ ሕዝብ ሐሳባቸውን ሰምቶ የመምረጥ ዕድል እንዲያገኝ ግንዛቤ

ከመስጠት አንፃር የማመቻቸት እንጂ እዚህ ስለቀረበ ማኅበሩ ዕውቅና ሠጥቶአል ማለት አይደለም፡፡ ማኅበሩ ለማንኛውም አካል ዕውቅና በክልከላ ከሚያስቀምጣቸው መካከልም ሊሰመርበት የሚገባው አንዱ ጉዳይ ይህ ነው፡፡

ባጠቃላይ የማኅበሩ ድርሻ ሰዎች የእያንዳንዱን አቋም እንዲያውቁ ማድረግ ነው፡፡ ከመንግሥት ፣ከምርጫ ቦርድ፣ ከሲቪክ ማኅበራት እና ከመገናኛ ብዙኃን የሚጠበቀውም ተመራጮች አቋማቸውን የሚያሳውቁበት መድረክ ማመቻቸት ነው፡፡ በአንቀጽ ፪.፳ ላይ የተቀመጠው ይህንን ነው ዕድል መፍጠር የሚለውም ሁሉም እኩል ታውቆ ሰው የቱ ይጠቅመኛል? ለሀገር የሚጠቅመው የቱ? ነው ብሎ ሚዛን ላይ እንዲያስቀምጥ ዕድል ይሰጣል የሚል ነው፡፡ ስለሆነም እንደ ቤተ ክርስቲያን፣ እንደ አንድ ተቋምም ይህንን ድርሻ እንወጣለን ማለት ነው እንጂ ይሁንታ እና ዕውቅና ከመስጠት ጋር የተገናኘ አይደለም፡፡

ሌላው በመመሪያው ላይ ከተቀመጡት አንቀጾች መካከል በማኅበሩ በአመራርነት እና በአባልነት ደረጃ በፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ መሳተፍ የሚችሉና የማይችሉ ተብሎ በተቀመጠው አንቀጽ ላይ ማኅበሩ በፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ሲል አንቀጽ ፫.፪ ላይ እንደተጠቀሰው የማኅበሩ መዋቅር፣ መልካም ስም፣ ሀብት እና ንብረት ለማንኛውም የፖለቲካ ሥራ እንዲውል አይፈቅድም ማለት ነው፡፡ ይህንን የሚያስፈጽሙ አካላት እነማን ናቸው? ብሎ ነው በዋናነት ያሰመረበት፡፡ ማንኛውም አካል ወይም ዜጋ በፖለቲካ ጉዳይ የመሳተፍ መብት ቢኖረውም ስለ ማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ሲባል ግን ተለይተው ይህንን መብት የተከለከሉ አካላት አሉ፡፡

እነዚህም ከሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ ያለውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚመራው የሥራ አስፈጻሚ ጉባኤ አባላት፣ ከሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ ያሉ ማዕከላትን በሰብሳቢነት፣ በምክትል ሰብሳቢነትና በጸሓፊነት የሚመሩ አካላት፣ በጽ/ቤት ደረጃ ያሉ በየሀገረ ስብከቱ ባለው መዋቅር እንደ ማዕከል የሚመሩ በሀገር ውስጥ እና በሀገር ውጪ ያሉ ማዕከላት፣ ወረዳ ማዕከላት፣ ግቢ ጉባኤያት፣ ኤዲቶርያል ቦርድ፣ ኦዲትና ኢንስፔክሽን፣ የማኅበሩ ሚዲያዎች እና መምህራን ናቸው፡፡ ክልከላው በዐደባባይ የፖለቲካ አቋማቸውን እንዳያራምዱ፣ ምልክቶችን እንዳይዙ እንዲሁም የፖለቲካ አቋምን እንዳያስተጋቡ የሚሉ ጉዳዮችንም በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡ ይህን በተመለከተ አባላቱ ታች እስካለው መዋቅር ድረስ ደብዳቤም ደርሶአቸዋል፡፡ ከላይ በዝርዝር ከተቀመጡት አካላት ውጪ ያሉ የማኅበሩ አባላት ግን በማንኛውም እነሱ በፈለጉት እና በመረጡት የፖለቲካ ፓርቲ የመሳተፍ፣ የመደገፍ የመምረጥ፣ የመመረጥ መብት አላቸው፡፡

ከዚህ ቀደም በማኅበሩ በአመራርነት ላይ የነበሩ ከአመራርነት ከለቀቁ በኋላ የተለያየ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ሲገቡ ከማኅበረ ቅዱሳን ጋር አይይዞ ማየት እንዲሁም የማኅበሩ አቋም ነው በሚሉ ብዥታዎች ዙሪያ ማኅበሩ መልስ ሳይሰጥ ቆይቷል አሁን ግን በመመሪያው ተካቷል፡፡ ‹‹የማኅበረ ቅዱሳን ሥራ አስፈጻሚ አባላት በፖለቲካዊ ጉዳይ ላይ በአባልነት አይገቡም ሲባል መቼ? የሚለውን ብዙ ሰዎች አይረዱትም፡፡ አንዳንዶቹ በአንድ ወቅት በማኅበረ ቅዱሳን ሥራ አስፈጻሚ ውስጥ ሲያገለግል የነበረና አባል ዕድሜ ልኩን ፖለቲካ ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ ይመስላቸዋል፡፡ በፊትም አሁንም ያለው መመሪያ የሚለው በማኅበረ ቅዱሳን በየትኛውም መዋቅር ላይ ያሉ የተከለከሉ አባላት የሚከለከሉት ከላይ በተጠቀሱት የአገልግሎት መደብ ላይ በሚያገለግሉበት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ከዚህ ወጥተው በፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ወደ ማኅበሩ ተመልሰው መጥተው በተከለከለው መደብ ላይ ማገልገል ቢፈልጉ በመጀመሪያ ከፖለቲካ አባልነት ወጥተው ራሳቸውን ከአባልነት አግልለውና ነፃ አድርገው መምጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንን ብዥታም ለአባላቱ ግልጽ ተደርጓል፡፡

# አለቃ ኀሩይ ተ/ሃይማኖት ከ፲፰፻፺፯ - ፲፱፻፷፮ ዓ.ም

**በመጽሐፈ ሲራክ**



አለቃ ኀሩይ ተ/ሃይማኖት

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አዕማድ ሆነው ሲያገለግሏት የኖሩ እና የሚኖሩ የብዙ ሊቃውንት መምህራን ባለቤት ናት:: እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ በልጅነት ሕይወታቸው ከቤተሰቦቻቸው እና ከቀዬአቸው ርቀው በመሄድ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ለመማር ብዙ ዋጋ ከፍለው ትልቅ ደረጃ ላይ የደረሱ ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም:: በአብነት ትምህርት ቤት ሕይወታቸው ከራሳቸው አልፈው ወንበር በመዘርጋት ብዙዎችን የቤተ ክርስቲያን ልጆች በማፍራት አገልግሎቱ እንዲቀጥል ወርቃማ አሻራቸውን ያሳረፉ ብዙዎች ናቸው:: በነበራቸው የአገልግሎት ዘመናት ሁሉ ደሞዝ ሳይቆረጥላቸው፣ ቀለብ ሳይሰፈርላቸው ቤተ ክርስቲያንን በትሩፋት ሲያገለግሉ ኖረዋል::

በተሰጣቸው የዕድሜ ዘመን ሁሉ የቤተ ክርስቲያንን እምነት፣ ሥርዓት እና ትውፊት አስጠብቀው ለቀጣዩ ትውልድ ከማስተላለፍ አንጻር ሊቃውንቶቻችን ዘመን የማይሽረው ሥራ ሲሰሩ ኖረዋል:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት፣ በሥነ ምግባር፣ በትውፊቱ ጠንካራ ሆና እንድትቀጥል፤ ዘመን አመጣሹን ማዕበል ሁሉ ተቋቁማ እንድታልፍ ገና ከጥዋቱ ጠንካራ የሃይማኖት መሠረት ጥለዋል:: ቤተ ክርስቲያን በመምህራን ለምልማ እንድትታይ የተጉ፤ ቤተ ክርስቲያንን የሚረከብ ጠንካራ ትውልድ ሲቀርጹ የኖሩ ሊቃውንቶቻችን የአብነት ትምህርት ቤቱ ምሰሶ ሆነው አልፈዋል::

ከእነዚህ የቤተ ክርስቲያን ብርቅዬ ሊቃውንት መካከል አንዱ የሆኑትን አለቃ ኀሩይ ተ/ሃይማኖትን የሕይወት ታሪክ ለ‹‹ቤተ አብርሃም›› በሚሆን መንገድ አዘጋጅተነዋል ተከታተሉን::

አለቃ ኀሩይ ተ/ሃይማኖት ከእናታቸው ከወ/ሮ ሸዋረገድ ቢተውና ከአባታቸው ከቄስ ተ/ሃይማኖት ሲሳይ በ፲፰፻፺፯ ዓ.ም በሸዋ ክ/ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ አንጎለላ ኪዳነ ምሕረት ተወለዱ:: የልጅነት ሕይወታቸውን በተወለዱበት አካባቢ ከብት በመጠበቅ ያሳለፉት አለቃ ኀሩይ በአንጎለላ ኪዳነ ምሕረት በጊዜው የንባብ መምህር

ከነበሩት ከመምህር አባ ወንድሙ ዘንድ በመሄድ የንባብ፣ የዳዊትና የግብረ ዲቁና ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በ፲፱፻፷ ዓ.ም በ፲፩ ዓመታቸው ከአቡነ ማቴዎስ የዲቁና ማዕረግ ተቀብለዋል።

ለመንፈሳዊ ትምህርት ከነበራቸው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ በዚያ ሳይወሰኑ የተወለዱበትን መንደር ትተው በሸዋ ክ/ሀገር በሚገኘው የዜና ማርቆስ ገዳም በመሄድ ግብረ ትሕትና ከነበራቸው ከመምህር አባ ሀብተ ጊዮርጊስ ዘንድ የዜማ ትምህርት ጾመ ድጓን አጠናቀዋል። ከዚያም የቃለ እግዚአብሔር ትምህርት በሰፊው ወደ ሚናኝበት ጎንደር ክ/ሀገር በመሻገር በቤተልሔም ልዩ ስሙ ሾላ ጊዮርጊስ ከሚባል ደብር ከነበሩት ከመምህር ገብረ ሕይወት ዘንድ ጾመ ድጓ፣ ድጓና ምዕራፍ ተምረው አጠናቀው በቤተልሔም አስመስክረዋል። ከዚያም በጎንደር ክ/ሀገር ስማዳ ልዩ ስሙ አጅ ኪዳነ ምሕረት ከምትባል ቦታ ለአራት ዓመታት በመምህርነት ቆይተዋል።

አለቃ ጎሩይ ሐሳባቸው በአብነት ትምህርት ቤት የሚቀራቸውን መንፈሳዊ ትምህርት ጨርሶ መዝለቅ ነበርና መምህርነቱን በመተው እዚያው ስማዳ ልዩ ስሙ አርባዕቱ እንስሳ ከሚባል ቦታ ከታወቁት የቅኔ መምህር ምሥራቅ ዘንድ የቅኔ ትምህርታቸውን ተምረው ቅኔ እያስነገሩና እየዘረፉ ቆይተዋል። ከዚያም ወደ በለሳ በመሄድ ልዩ ስሟ አጣሌ ማርያም ከምትባል ቦታ ከታወቁት የአቋቋም መምህር መምህር ማስረሻ ዘንድ የአቋቋም ትምህርታቸውን በመማር አስመስክረዋል። ወደ ሰቆጣ መድኃኔ ዓለም ደብርም በመሄድ ከታወቁት የቅኔ መምህር ከመምህር ኤልሳዕ ዘንድ ተቀምጠው የተማሩትን በማጠናከር ለጥቂት ጊዜ ቆይተዋል።

ከሰቆጣ መድኃኔ ዓለም ወደ ሰሜን ቤተ አልቦ ሚካኤል በመሄድ ከመምህር አባ ኀይለ ጊዮርጊስ ዘንድ መዝገብ የቅዳሴና የዝማሬ የመዋሥዕት ተምረዋል። ከዚህም በተጨማሪ ከመምህር ቀለመወርቅ ዘንድ ዝማሬ መዋሥዕቱን አጠናቀው አስመስክረዋል። ከዚህ ቀጥለው ጎንደር መካነ ኢየሱስ በመሄድ መጻሕፍተ ብሉያትን በመማር አጠናቀዋል። በጠቅላላው በጎንደር ክፍለ ሀገር ጾመ ድጓ፣ ድጓ፣ ዝማሬ መዋሥዕት፣ መዝገብ ቅዳሴ፣ ቅኔና መጻሕፍተ ብሉያትን በመማርና በማስተማር ለሃያ አምስት ዓመታት ከቆዩ በኋላ ሀገሪቱን ወርሮ የነበረው የጣሊያን ሠራዊት ሀገሪቱን ለቆ ሲወጣ በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ተማሪዎቻቸውን በማስከተል ወደ ትውልድ ሀገራቸው ሸዋ ክፍለ ሀገር ተመልሰው በማስተማሩ ወንበር ዘርግተው ሲያስተምሩ ቆይተዋል።

**የሕይወት ታሪካቸውን እንዲነግሩአቸው ሰዎች በጠየቁአቸው ጊዜ ‹‹ምን ታሪክ አለኝና ትጠይቁኛላችሁ በዚህ ዓለም ላይ ታሪክ ሠሪው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ይልቁንስ ሃይማኖታችሁን አጠንክራችሁ ጠብቁ››**

በሕይወታቸው ሙሉ በቤተ ክርስቲያን ወንበር ዘርግተው ሲያስተምሩ የቆዩትና ከቤተ ክርስቲያን አንዲትም ቀን ያልተለዩት መምህር በዚያው ዘመን የሕግ ባለቤታቸውን በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አግብተው ስድስት ሴቶች እና አምስት ወንዶች ልጆችን አፍርተዋል፡፡ ጎንደር ክ/ሀገር በነበሩበት ጊዜና ወደ ሸዋ ክፍለ ሀገር ከተመለሱ በኋላ የጀመሩትን የጸዋትወ ዜማና የጸሎት መጻሕፍትን በብራና ላይ የመጻፍ ሥራን ጨርሰው ለተለያዩ አድባራት እና ገዳማት ለአገልግሎት ይውሉ ዘንድ አበርክተዋል፡፡ መጻሕፍቶቻቸው ከሚገኙባቸው ገዳማት ውስጥ አንዱ ደብረ ሊባኖስ ገዳም አንዱ ነው፡፡

ወንበር ዘርግተው በርካታ ተማሪዎችን በማስተማር ሲተጉ የነበሩት ታላቁ መምህር አለቃ ጎሩይ ማዕረገ ቅስናን ከተቀበሉ በኋላ በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም ‹‹እንተ ይእቲ ጽርሐ አርያም አንጎለላ ኪዳነ ምሕረት መካነ ልደቱ ወጥምቀቱ ለዳግማዊ ሚኒልክ›› በሚል ስያሜ ለምትጠራው ለአንጎለላ ኪዳነ ምሕረት ደብር አለቃ ሆነው ተሹመዋል፡፡ በዚያም በነበራቸው መንፈሳዊ አገልግሎት ወንበር ዘርግተው ከሚያስተምሩት ተማሪ ጎን ለጎን የአጥቢያውን ካህናትና ምእመናን ልጅ አዋቂ ሳይሉ ግብረ ትሕትና በተሞላበት መንፈስ ሲመሩ ቆይተዋል፡፡

አለቃ ጎሩይ ለአንጎለላ ኪዳነ ምሕረት ደብር ከተሾሙበት ጊዜ ጀምሮ በመቃኞ ያለችውን የእመቤታችንን ታቦት ወደ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን እንደትገባ ከነበራቸው መንፈሳዊ ቅንዓት የተነሣ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ብዙ ደክመዋል፣ ወጥተው ወርደዋል፡፡ በአካባቢው ያሉትን ተወላጆች በማስተባበር ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንዋን በማሠራት ጽላቷ ከመቃኞ ወጥታ ወደተሠራላት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን እንደትገባ አድርገዋል፡፡ አለቃ ጎሩይ እንደቀደሙት ደጋግ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የራሳቸውን ክብርና ዝና መናገር የማይፈልጉ መምህረ ትሕትና ናቸው፡፡ ለዚህ ማረጋገጫው በሕይወት በነበሩበት ወቅት የሕይወት ታሪካቸውን እንዲነግሩአቸው ሰዎች በጠየቁአቸው ጊዜ ‹‹ምን ታሪክ አለኝና ትጠይቁኛላችሁ በዚህ ዓለም ላይ ታሪክ ሠሪው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ይልቁንስ ሃይማኖታችሁን አጠንክራችሁ ጠብቁ›› በማለት እንደመለሱላቸው የሚያውቁአቸው ያነሳሉ፡፡

አለቃ ጎሩይ በአንጎለላ ኪዳነ ምሕረት ደብር በአለቅነት ከዚያም በተጨማሪ ፊት የጀመሩትን ወንበር ዘርግተው የአብነት ትምህርቱን በማስተማር ብዙ ተማሪዎችን ያፈሩ ሲሆን በቦታው ለ፴፬ ዓመታት ያህል ካገለገሉ በኋላ ‹‹አዳም ሆይ መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ ›› ተብሎ እንደተነገረው በአደረባቸው ሕመም ምክንያት ታኅሣሥ ፴ ቀን ፲፱፸፮ ዓ.ም በተወለዱ በ፸፱ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡

*የአባታችንን ነፍስ ከደጋጎቹ ጎን ያኑርልን!*

# “የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ለመበረዝ በተነሡ ቡድኖች ላይ እስካሁን የተወሰደ ተጨባጭ ርምጃ የለም”

*በካሣሁን ለምለሙ*

*- ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ (የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)*

*ክፍል ሁለት*

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ቃለ መጠይቅ የመጀመሪያ ክፍል ባለፈው እትማችን ላይ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ በዚህ እትማችን ደግሞ ክፍል ሁለትን ይዘንላችሁ ቀርበናል፡፡ ትከታተሉ ዘንድ ግብዣችን ነው፡፡***

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** *በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት የሚኙት ‹‹የቅባት እምነት›› አራማጆች በርስዎ ሀገረ ስብከት ላይ ያደረሱት ተፅእኖ ካለ ቢገልጹልን?*

***ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፡-*** ሀገረ ስብከታችን ከምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ጋር የሚዋሰን በመሆኑ ቀሳጥያኑ በተለይም በደጋ ዳሞት በኩል እየገቡ ሕዝበ ክርስቲያኑን ሊከፋፍሉና ባዕድ አስተምህሯቸውን ሊያስፋፉ ሲሞክሩ ጥብቅ ቁጥጥርና ክልከላ በማድረግ በአካባቢው እንዳይንቀሳቀሱ ስናደርግ ቆይተናል፡፡ የአካባቢው ምእመናንም ሆኑ ካህናቱ ችግሩን በደንብ የተረዱ፣ እምነታቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸውና ሊደርስባቸው የሚችለውን ጫና በመገመት በሀገረ ስብከታችን ከሙከራ የዘለለ የተጠናከረ እንቅስቃሴ አያደርጉም፡፡ በሀገረ ስብከታችን ውስጥ ሰርገው በሚገቡበት ወቅት በተቆጡ ምእመናንና አገልጋዮች አማካይነት ችግር ውስጥ እንዳይገቡ እኔም ምእመናንና ካህናትን በመሰብሰብ ችግር ሳይፈጠር በዓይነ ቁራኛ ብቻ ተከታትለው በሰላም እንዲወጡ የማድረግ ሥራ ብቻ እንዲሠሩ እነግራቸዋለሁ፡፡ አልፎ አልፎ ወደ ሀገረ ስብከታችን በሚመጡበት ወቅት በምእመናን በሚደርስባቸው ጫና ምክንያት አፍረውና ተሸማቅው ይመለሳሉ፡፡

በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት በሕዝቦች መካከል ሊፈጥር የሚችለውን ችግር አስቀድመው የተረዱት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርእሰ መስተዳድር የሆኑት



ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

ክቡር አቶ አገኘው ተሻገርም የካቲት ፪ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ለቅዱስ ሲኖዶስ ደብዳቤ ጽፈዋል፡፡ እርሳቸው የጻፉት ደብዳቤም በጣም አስፈላጊና የክልሉ መንግሥት ምን ያህል ለጉዳዩ ትኩረት እንደሰጠው ያመላከተ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ የክልሉ መንግሥት በዚህ ምክንያት ችግር ከመፈጠሩ በፊት ጉዳዩን ተረድቶ ለመፍታት ያደረገው ጥረት የሚመሰገንና ሌሎች አካባቢዎችም ከዚህ አርቆ አሳቢነት ሊማሩ ይገባል፡፡ የክልሉ መንግሥት ላደረገው አስተዋፅኦ ለቅዱስ ሲኖዶስ በጻፍኩት ደብዳቤ ላይ አመስግኛለሁ፣ ለወደፊቱም አመሰግናለሁ፡፡ የክልሉ መንግሥትና የእኔ ደብዳቤ ለቅዱስ ሲኖዶስ ገብቷል፡፡ በቀጣይም ከአባቶችና ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር በመሆን ችግሩን በሰከነ መንገድ ለመፍታት ያለሠለሰ ጥረት አደርጋለሁ፡፡

በሃይማኖትና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጉዳይ የሚደራደር ትውልድ ሊኖር አይገባም፡፡ መንግሥት የቤተ ክርስቲያኗ አንድነትና ሥርዓት መጣስ አሳስቦት ችግሩ በሰላማዊ

*መንገድ እንዲፈታ ጥረት ካደረገ እኛ ቤተ ክርስቲያንን እና ምእመናንን የምናስተዳድር የቤተ ክርስቲያን አባቶች ደግሞ ችግሩ በሰከነ መንገድ እንዲፈታ መታለፍ ያለበትን ውስብስብ መንገድ ሁሉ ማለፍ ይጠበቅብናል፡፡ የክልሉ መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን እንደዚህ ካለ አሳሳቢ ችግር እየጠበቃት በመሆኑ እኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆችም ከክልሉ መንግሥት ጎን በመቆም የድርሻችን ልንወጣ ይገባል፡፡*

*አሁን የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ያለበት ሁኔታ በጣም የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ ነው፡፡በአካባቢው የተወሰኑ ‹‹መነኰሳት›› ነን የሚሉ ግለሰቦች ተነሥተው ራሳቸውን ‹‹ፓትርያርክና ሊቀ ጳጳስ›› አድርገው ሾመዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ስያሜም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወደ ‹‹ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን›› ቀይረውታል፡፡ እነርሱ በራሳቸው የሰየሟቸው ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ንብረቶች ናቸው፡፡ ይህንን ግፍ የተመለከቱ ምእመናንም በጣም እያዘኑና እያለቀሱ ይገኛሉ፡፡ እኔ ለቅዱስ ሲኖዶስ ደብዳቤ የጻፍኩት ስለ አካባቢው ችግር በርቀት ከሰው በሰማሁት ተነሣሥቼ ሳይሆን በአካባቢው ተገኝቼ ችግሩን ተዘዋውሬ ከተመለከትኩ በኋላ ነው፡፡*

*ባለፈው ጥቅምት ወር በነበረው የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ላይ የችግሩን ጥልቀትና ሥፋት በሚገባ አስረድቻለሁ፡፡ ራሳቸውን ‹‹ፓትርያርክና ሊቀ ጳጳስ›› አድርገው የሾሙ ግለሰቦችም ‹‹ክህነት እንሰጣለን” በሚል ሕዝቡን እየሰበሰቡ ለሁሉም ሰው እነርሱ ‹‹ክህነት›› ያሉትን እያደሉ እንደሆነ አረጋግጫለሁ፡፡ ይህ ድርጊት እንኳን ለኔ ለመንጋው ጠባቂ ይቅርና ለማንም ሌላውም ሰው እጅግ ያሳዝናል፤ ያስለቅሳልም፡፡ ‹‹በእግዚአብሔር ጸጋ ተሹመናል›› የሚሉት ግለሰቦች የክብር ቆብ የሆነውን አስኬማ እንዳይጠቀሙ፣ ልብሰ ተክህኗቸውን እንዲያወልቁ እና ዘመናቸውን በሙሉ በመረጡትና በወደዱት ገዳም ውስጥ ሆነው የንስሓ ዕድሜያቸውን እንዲጨርሱ ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው መሠረት አፈጻጸሙንም ሊከታተሉት የሚገባቸው የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ማርቆስ ነበሩ ነገር ግን እስካሁን ድረስ ችግሩ እንዲፈታ ያደረጉት ጥረት የለም፡፡ ብፁዕነታቸው የሀገረ ስብከታቸውን ችግር ቶሎ እንዲያስተካክሉ በተደጋጋሚ ሐሳብ ሰጥቻለሁ፤ ቤተ ክርስቲያን ስትፈርስ ቆመው እንዳይመለከቱ ተናግሬአለሁ፡፡ የተሐድሶ የግብር ልጆችና ቤተ ክርስቲያናችን በተለያዩ ጊዜያት ያወገዘቻቸው ግለሰቦች ከክፉ ተግባራቸው ጋር በአካባቢው እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡ እነዚህም አካላት ባዕድ አስተምህሮን ያስተምራሉ፤ ሥልጠናም ይሰጣሉ፤ ካህናቱን ሳይቀር በእነርሱ መንገድ እንዲጓዙ ጥረት ያደርጋሉ፤ ካህናቱም ጉዳዩ ይመለከተዋል ለሚሉት አካል ሁሉ ችግሩ እንዲስተካከል በየጊዜው ይጮሃሉ፡፡ እኔም ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ ካህናትንም ሆነ ምእመናንን እየመከርኩ፣ እያጽናናሁ እንዲሁም እያስተማርኩ እገኛለሁ፡፡ ሰዎች በፈቃዳቸው ተሰባስበው የመንግሥትን ፈቃድ ካገኙ የራሳቸውን አዲስ ሃይማኖት ሊመሠርቱ ይችላሉ፡፡ እሱ ችግር የለውም፤ ምክንያቱም ሰው የመሰለውንና ያመነበትን ሃይማኖታዊ አስተምህሮ መከተል ይችላልና፡፡ ነገር ግን በእኛ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ ሌላ የተለወጠ ሃይማኖት እመሠርታለሁ ማለት ግን አይቻልም፤ ወንጀልም ነው፡፡ በዚህ ሀገረ ስብከት የተፈጠረው ችግርም ይኸው ነው፡፡ የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ችግር ለረጅም ጊዜ የቆየ በመሆኑ እኔም ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኝ በተደጋጋሚ ለቅዱስ ሲኖዶስ ሪፖርት አቅርቤአለሁ፡፡ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድም በቅርቡ ጉዳዩ መፍትሔ አግኝቶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በቀደመ አስተምህሮዋ ትቀጥላለች፤ ልማቷም ይፋጠናል ብዬ አስባለሁ፡፡*

*ብፁዕነታቸው ብፁዕ አቡነ ማርቆስ በሀገረ ስብከታቸው ላይ እያጠፉት ባለው ጥፋት በካህናትና በበርካታ ምእመናን*

ዘንድ ወቀሳ ቀርቦባቸዋል፡፡ በጥንታዊው ገዳም ዲማ ጊዮርጊስን ጨምሮ በጉንደ ወይንና በሌሎች አካባቢዎች እየተዘዋወሩ በሚያስተምሩበት ወቅት ከእውነተኛ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ውጭ የሆነውን በማስተማራቸውና የሥነ ምግባር ግድፈት ከማሳየታቸው ባሻገርም በሕዝቦች መካከል ቁርሾና መለያየትን በሚሰብኩበት ወቅት ማስጠንቀቂያ የሰጧቸውን ፖሊስ ሳይቀር በመገላመጥና ሕዝቡ ጥቃት እንዲያደርስ የማነሣሣት ሥራ ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ ሀገረ ስብከቱ ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር ጉድለት ያለበት በመሆኑ በርካታ ካህናትና መምህራን ወንጌል ከአገልግሎታቸው ያለ በቂ ምክንያት ታግደዋል፤ ተሰናብተዋልም፡፡ ለመታገዳቸው ምክንያት ሆኖ የሚቀርበው ደግሞ ‹‹የቅባት እምነትን ካልተቀበላችሁ” የሚል ነው፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና የማኅበረ ቅዱሳን ሚዲያ ክፍል ችግሩ እንዲፈታ እያደረጋችሁ ላላችሁት አስተዋፅኦ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡ እኔ ደብዳቤ ከመጻፍ አልፌም ገና ክስ እመሠርታለሁ፡፡ ለሃይማኖቴ እስከመጨረሻው ድረስ እታመናለሁ፡፡ ከልጅነት እስከ ዕውቀት፣ ከዲቁና እስከ ጵጵስና አስተምራ ኮትኩታ ለዚህ ያበቃችኝ ቤተ ክርስቲያን ችግር በገጠማት ወቅት እርሷን ከችግር ለማዳን አስፈላጊውን ሁሉ አደርጋለሁ፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ዓለም አቀፋዊትና ሐዋርያዊት የሆነች መሰልና ወደር የሌላት፣ በሥርዓቷ፣በቅርሶቿና በቀደምትነቷ ዓለም የሚቀናባት እንዲሁም መርምሮ ያልደረሰባት ናት፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ካላት ዕውቅና ባሻገር በየጊዜው በሚካሄዱ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ጭምር ካላት የጥንታዊነት ባሕርይ የተነሣ መጀመሪያ በሥርዓተ ጸሎት እንድትከፍት ይደረጋል፡፡ ስለዚህም ዓለም አቀፍፋዊ ክብር ያላት ቤተ ክርስቲያናችን አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በገባችበት በዚህ ወቅት ማንኛውም ሰው ዝም ሊል አይገባም፤ ይሉኝታ ሊኖረንም አይገባም፤ ችግሩን በፍጥነት ማስተካከል ይኖርብናል፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት በተፈጠረው ችግር መነሻነት ለቅዱስ ሲኖዶስ ደብዳቤ ከጻፉ በኋላ ያገኙት ምላሽ ምንድን ነው?

***ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፡-*** ደብዳቤውን ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት ካስገባሁ በኋላ ተሰብስበው በአጭር ጊዜ ውስጥ ለችግሩ መፍትሔ እንደሚሰጡ ነግረውኛል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩ ቶሎ መፍትሔ እስካልተሰጠው ድረስ ቤተ ክርስቲያንን ከጥፋት ለመታደግ አቅሜ የፈቀደውንና ማድረግ ያለብኝን ሁሉ አደርጋለሁ፡፡

ጉዳዩ እኔን ብቻ ሳይሆን መላው ሕዝበ ክርስቲያንና አገልጋዮችን ያስጨነቀ ነው፡፡ በምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ያለችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በጣም ተረብሻለች፡፡ በሃይማኖታቸው ምክንያት ከአገልግሎት የታገዱና የወር ደመወዛቸው የተቀረጠባቸው በርካታ ካህናትና መምህራን በመኖራቸው ለከፍተኛ እንግልት እየተዳረጉ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ችግር ባለባት በዚህ ጊዜ ያሉትን ሊቃውንት ማሳደድና ማንገላታት ተገቢ ካለመሆኑም በላይ አሁን ላይ ያለው ችግር ቤተ ክርስቲያንን ያለ አገልጋይ የሚያስቀር፣ በበረት ያሉ በጎችንም የሚበትን ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን አንድ ሊቃውንት ለማፍራት ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድበት ይታወቃል፡፡ እነዚህን ሊቃውንት ተንከባክቦና ጥያቄያቸውን መልሶ መያዝና በአገልግሎት ተግተው እንዲቀጥሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ጥልቅና ውስብስብ ችግር ቅዱስ ሲኖዶስ ተረድቶ የማያዳግም የርምት ርምጃ ወስዶ ዘላቂ መፍትሔ ይሰጣል ብዬ አምናለሁ፡፡

ይህ ችግር የዶግማና የሥርዓት ጥሰትን መነሻ ያደረገ ስለሆነ ጉዳዩን በጥንቃቄ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ የቀናች ሃይማኖታችን እንዳትጠፋና እንዳትበረዝ ሁሉም የሚመለከተው አካል በትጋት በጋራ ሊሠራ ይገባል፡፡ ከዚህ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በእኔ አቅም መደረግ ያለበትን ሁሉ የማድረግ ሲሆን ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት የጻፍኩትን ደብዳቤ አያይዤ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግሥት ደብዳቤ እጽፋለሁ። ቤተ ክርስቲያናችን የባዕዳን መነገጃ ተቋም ልትሆን አይገባም። የማይቀየር የማይለወጥ ሥርዓትን ሠርታ ያስቀመጠችና በሥርዓቷም እየተጠቀመችበት ያለች እንዲሁም በውስጧም ዶግማዋንና ቀኖናዋን ተንቅቀው ሚያውቁ ሊቃውንት ያሏት ናትና ሊቃውንቷ ይህንን ጉዳይ በዝምታ አያልፉትም። ስለዚህ ይህ ባለበት ሁኔታ ለምን በባዕዳን አስተምህሮ ትበረዛለች? እነዚህ የቤተ ክርስቲያናችንን እውነተኛ አስተምህሮ ሊበርዙ የሚሯሯጡ ጥቂት ግለሰቦች ከክፉ ድርጊታቸው ቢቆጠቡ መልካም ነው።

**ሃይማኖታችንን ሳትበረዝና ሳትከለስ ለመጪው ትውልድ ለማስረከብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ አለበት። የሕዝበ ክርስቲያኑ አንድነት እንዲጠበቅና በሃይማኖት የተነሣ ጠብና እልቂት እንዳይኖር ሁላችንም የየድርሻችን ልንወጣ ይገባል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን የባዕዳን አስተምህሮ እንዳያጠቃት ማድረግ ያለብንን ሁሉ ማድረግ አለብን።**

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** *የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ችግር ሳይፈታ እስከ ዛሬ ድረስ የቆየበት ምክንያት ምንድን ነው ይላሉ?*

***ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፡-*** ችግሩ እንዲፈታ ቅዱስ ሲኖዶስ በተደጋጋሚ ቆራጥ ውሳኔ አሳልፏል። ቢሆንም ግን የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ለመበረዝ በተነሡ ቡድኖች ላይ የተወሰደ ተጨባጭ የርምት ርምጃ የለም። ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ቡድኖች የምትቀጣበት የፖሊስ ኃይልም ሆነ ፍርድ ቤት የሏትም። እነዚህ ኃይሎችም ‹‹ሰው የወደደውን እምነት መከተል ይችላል›› የሚለውን ሀሳብ በተሳሳተ መንገድ የተረዱ ኃይሎች በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁከትና ብጥብጥ የሚፈጥሩት ከላይ በተጠቀሰው እሳቤ መሠረት “የሕግ ከለላ አለን ብለው ስለሚያስቡ” ነው። ርግጥ ነው ሰው የወደደውን ሃይማኖት የመከተል መብት አለው ነገር ግን በእኛ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ የቤተ ክርስቲያንን ዕውቀትና ንብረት እየተጠቀሙ ከሆነ ግን ከወንጀል በላይ ወንጀል ነው። ችግሩ ከፍቶ በመላው ጎጃም ያሉትን ሕዝበ ክርስቲያኖች እንዳያጠቃ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ውሳኔዎችና ውግዘቶች ተላልፈዋል። በዚህ ሳቢያ ችግሩ የረገበ ይመስልና ከጊዜ በኋላ ደግሞ አጥፊ ቡድኑ አይዞህ ባይ ሲያገኝ የቅሳጤ ሥራውን መልሶ ይጀምራል።

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** *ብፁዕ አባታችን ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?*

***ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፡-*** ሃይማኖታችንን ሳትበረዝና ሳትከለስ ለመጪው ትውልድ ለማስረከብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ አለበት። የሕዝበ ክርስቲያኑ አንድነት እንዲጠበቅና በሃይማኖት የተነሣ ጠብና እልቂት እንዳይኖር ሁላችንም የየድርሻችን ልንወጣ ይገባል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን የባዕዳን አስተምህሮ እንዳያጠቃት ማድረግ ያለብንን ሁሉ ማድረግ አለብን።

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** *ብፁዕ አባታችን ለነበረን ቆይታ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ።*

***ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ፡-*** እኔም በጣም አመሰግናለሁ፤ ተባረኩ።

# ዐቢይ ጾም (ጾመ ሁዳዴ)

በእህተ ሚካኤል

*ልጆች! ባለፉት ሁለት እትሞቻችን በዐቢይ ጾም (በጾመ ሁዳዴ) ውስጥ ከሚገኙ ሳምንታት እና መጠሪያዎቻቸው ውስጥ ከዐቢይ ጾም የመጀመሪያው ሳምንት ጀምሮ ‹‹ዘወረደ››፣ ‹‹ቅድስት››፣ ‹‹ምኩራብ››፣‹‹መጻጉዕ››፣‹‹ደብረ ዘይት›› እና ‹‹ገብር ኄርን›› ስያሜያቸውንና ታሪካቸውን ነግረናችሁ ነበር። ስያሜያቸውንና ታሪካቸውን በደንብ እንደተረዳችሁ ተስፋ እናደርጋለን። እነሆ በዚህ ዝግጅት ደግሞ ስለ ‹‹ኒቆዲሞስ››፣ ‹‹ሆሣዕና›› እንዲሁም ስለ ሰሙነ ሕማማት ይዘንላችሁ ቀርበናል ተከታተሉን።*

## 7. ኒቆዲሞስ

ልጆች! ሰባተኛው የዐቢይ ጾም ሳምንት ‹‹ኒቆዲሞስ›› በመባል ይጠራል። ኒቆዲሞስ ከፈሪሳውያን ወገን ሲሆን ኢየሩሳሌም ውስጥ ካሉት የአይሁድ አለቆች እና መምህራን አንዱ ነው። ኒቆዲሞስ የብሉይ ኪዳንን ትምህርት ጠንቅቆ የሚያውቅና መምህር ፣ በሀብት ደረጃ ከፍ ያለ ሀብት ያለው ከመሆኑም በላይ የአይሁድ አለቃና ባለ ሥልጣንም ነው። ኒቆዲሞስ ወንጌልን ለመማር ከአይሁድ ቀድሞ በሌሊት ወደ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣ መምህረ አይሁድ ነው። (ዮሐ ፫፥፩–፳፩)

ኒቆዲሞስ በሌሊት ወደ ጌታችን ከመጣ በኋላ የተለያዩ ጥያቄዎችን ጠይቆታል። ልጆች! ኒቆዲሞስ ጌታችንን ከጠየቃቸው ጥያቄዎችና ጌታችን ከመለሰለት መልሶች መሀከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

ኒቆዲሞስ ፦ ‹‹መምህር ሆይ ልታስተምር ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርገውን ይህ ተአምር ሊያደርግ የሚችል የለምና›› አለው

ጌታችን ኢየሱስም መልሶ ፦ ‹‹ እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ዳግመኛ ያልተወለደ ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማየት አይችልም›› አለው።

ኒቆዲሞስም ፦ ‹‹ሰው ከሸመገለ በኋላ ዳግመኛ መወለድ እንደምን ይችላል? ዳግመኛ ይወለድ ዘንድ ወደ እናቱ ማኅፀን ተመልሶ መግባት ይችላልን?›› አለው።

ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ እውነት እውነት እልሃለሁ ዳግመኛ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነውና።›› በማለት ለኒቆዲሞስ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት በሚገባ አስተምሮታል።

ልጆች! ኒቆዲሞስ የብሉይ ኪዳን አዋቂ የኦሪት መምህር ቢሆንም በሌሊት ወደ ጌታችን እየሄደ ወንጌልን ለመማርና በክርስቶስ ለማመን በቅቷል። ወገኖቹ አይሁድ ጌታን ሰቅለው በገደሉት ጊዜም ከክፉ ሥራቸው ጋር ያልተባበረ ጻድቅ ሰው ነበረ። ከአርማትያሱ ዮሴፍ ጋር በመሆንም ወደ ሀገረ ገዢው ጲላጦስ በመሄድ የጌታችንን ቅዱስ ሥጋ ከመስቀል አውርዶ ይቀብረው ዘንድ በመለመን ለራሱ ባሠራው አዲስ መቃብር ቀብሮታል ዮሐ ፲፱፥፴፱። ከዐቢይ ጾም ሳምንታትም ሰባተኛው ሳምንት ኒቆዲሞስ የሚባለው ኒቆዲሞስ የተባለው የአይሁድ መምህር ከጌታ ዘንድ ለመማር በሌሊት በመሄዱ ነው።

## 8. ሆሣዕና

ልጆች! የዐቢይ ጾም ስምንተኛ ሳምንት ሆሣዕና በመባል ይጠራል። ሆሣዕና ከስምንቱ የዐቢይ ጾም እሑዶች አንዱ ሲሆን ከትንሣኤ ቀድሞ የሚገኝ የመጨረሻው ሳምንት ነው። ሆሣዕና የእብራይስጥ ቃል ሲሆን ትርጉሙም

‹‹አቤቱ እባክህ አሁን አድን፣ አቤቱ እባክህ አሁን አቅና›› ማለት ነው:: እንዲሁም ሆሣዕና ማለት ‹‹መድኃኒት›› ማለት ነው:: በዚህ ቀን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ንጉሥ በአህያ ላይ ተጭኖ ኢየሩሳሌም በክብር የገባበት ቀን ነው::

ልጆች! በወንጌል ላይ ተጽፎ እንደምናገኘው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቢታንያ ተነስቶ ወደ ደብረ ዘይት ሲደርስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ጠርቶ ‹‹በፊታችሁ ወዳለች መንደር ሂዱ ያንጊዜም የታሰረች አህያ ከውርንጭላዋም ጋር ታገኛላችሁ፤ፍቱና አምጡልኝ ። ምን ታደርጋላችሁ? የሚላችሁ ቢኖርም ጌታቸው ይሻቸዋል በሉ ያን ጊዜ ይሰዱአችኋል›› አላቸው (ማቴ ፳፩፥፩–፫)

ሐዋርያትም እንደታዘዙት አህያዋን ከውርንጭላዋ ጋር ፈተው አመጡለት አጠገቡም ሲደርሱ ልብሳቸውን በአህያይቱ ላይ አንጥፈው ጌታችንን አስቀመጡት:: ጌታም በአህያይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ:: ልጆች! ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ የፋሲካን በዓል ለማክበር ከተለያዩ ሀገራት እና ከተማዎች የመጡ እንዲሁም ከሞተ እና ከተቀበረ አራት ቀን በኋላ ጌታ ከሙታን ያስነሳውን አልአዛርን ለማየት የተሰበሰቡ ብዙ ሕዝብ በኢየሩሳሌም ነበሩና የዘንባባ ዝንጣፊ በመያዝ (ዘንባባ የሰላም፣ የድል አድራጊነት ምልክት ነው::)፣ ልብሳቸውን በየመንገዱ ላይ በማንጠፍ ‹‹ሆሣዕና በአርያም በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው›› እያሉ ሕፃናት ሳይቀሩ ይዘምሩለት ነበር::

ነገር ግን ፈሪሳውያን በዚህ ጅግ በመበሳጨታቸው ጌታችንን ‹‹መምህር ሆይ ደቀ መዛሙርትህ እንዳይዘምሩ ተቆጣቸው›› አሉት:: ጌታችንም ‹‹ እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮሃሉ›› ብሎ መለሰላቸው (ሉቃ ፲፱፥፴፱):: ከዐቢይ ጾም ሳምንታትም ስምንተኛው ሳምንት ሆሣዕና የተባለበት ምክንያት ጌታችን በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በመግባቱ ነው::

ሰሙነ ሕማማት ፦ ልጆች! በዐቢይ ጾም ከሰርክ ሆሣዕና ጀምሮ እስከ ትንሣኤ ሌሊት ያሉት ዕለታት ሰሙነ ሕማማት በመባል ይጠራሉ:: ቤተ ክርስቲያን ከትንሣኤ በፊት ያለውን ሳምንት ሰሙነ ሕማማት በማለት ትዘክረዋለች:: ‹‹ሕማማት የሚለው ቃልም ‹‹ሐመ፣ ታመመ›› ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማሙ፣ እንግልቱና ሞቱ የሚዘከርበት፣ የሚነገርበት ሳምንት ነው::

ልጆች! ስለ ዐቢይ ጾም በጻፍነው በመጀመሪያው እትማችን ላይ ስለ ጾመ ሁዳዴ ስንነጋገር የዐቢይ ጾም የመጀመሪያው ሳምንት እና የመጨረሻው ሳምንት የተጨመሩ መሆናቸውን ነግረናችሁ ነበር አስታወሳችሁ? የጾሙ የመጀመሪያ ሳምንት ‹‹ጾመ ሕርቃል›› እንደሚባል እንዲሁም የጾሙ የመጨረሻው ሳምንት ‹‹ሰሙነ ሕማማት›› በመባል ስያሜያቸውን እንዳገኙ ነግረናችሁ ነበር:: ሰሙነ ሕማማት ጌታችን መድኃኒታችን ለሰው ልጆች ደኅንነት ሲል በሥጋው መከራ መቀበሉን የምናስብበት ሳምንት ነው::

የሰሙነ ሕማማት ዕለታት የተለዩ ናቸው:: በዚህ ሳምንት ከጸሎተ ሐሙስ በስተቀር ቅዳሴ አይቀደስም፣ ጸሎተ ፍትሐት (ለሞተ ሰው የሚደረግ ጸሎት) አይደረግም፣ ምሥጢረ ጥምቀት (ጥምቀተ ክርስትና) አይደረግም፤ መስቀል አንሳለምም፣ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ሳምንት ውስጥ የንግሥ በዓል አይደረግም::

ልጆች! በሰሙነ ሕማማት ሳምንት በሚገኙ ዕለታት የተለያዩ ክንውኖች የሚካሄዱ ሲሆን እነሱም የሚከተሉት ናቸው፦

አለመሳሳም - በሰሙነ ሕማማት መጨባበጥ፣ ትከሻ ለትከሻ ተገናኝቶ በተቀደሰ አሳሳም መሳሳም ክልክል ነው፤ ይህም ይሁዳ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ‹‹እኔ የምስመው እሱ ክርስቶስ ነውና›› ያዙት ብሎ በመሳም ጌታን ለአይሁድ አሳልፎ መስጠቱን በማሰብ ነው::

ሕጽበተ እግር - ‹‹ጸሎተ ሐሙስ›› በመባልም ይታወቃል::

ጌታችን በዚህ ዕለት በፍጹም ትሕትና ዝቅ ብሎ የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበበት፣ ምሥጢረ ቁርባንን ያከናወነበት ዕለት  በመሆኑ ስያሜውን ያገኘው ከዚያ ነው::

አክፍሎት -  በሰሙነ ሕማማት በዕለተ ዓርብ ከስግደት በኋላ እህል ቀምሰው እስከ እሑድ (ትንሣኤ) የሚጾመው ጾም አክፍሎት ይባላል:: አንዳንድ የበረቱ ሰዎች ደግሞ ሐሙስ በልተው እስከ ትንሣኤ የሚያከፍሉ አሉ::

ጉልባን - ጉልባን ከባቄላ ክክ እና ከተፈተገ ስንዴ ወይም ገብስ ጋር ተቀቅሎ የሚዘጋጅ ሲሆን የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ከቅዳሴ በኋላ ይበላል::

ጥብጣብ - በዕለተ አርብ (የስቅለት ዕለት) ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ሲሰግዱና ሲጸልዩ ከዋሉ በኋላ ወደቤት ከመመለሳቸው (ከቤተ ክርስቲያን ከመሰናበታቸው) በፊት ወደ ካህናት ቀርበው ኃጢአታቸውን ይናዘዛሉ(ይናገራሉ) ካህናቱም በወይራ ቅጠል ትከሻቸውን እየጠበጠቡ(ቸብ ቸብ እያደረጉ) የሚያዙአቸው ተጨማሪ ስግደት ነው::

ቀጤማ -  በስቅለት ማግሥት ቅዳሜ የሚታደል ቀጤማ (እርጥብ ሳር ነው):: በዚህ ዕለት ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ቃጭል እያቃጨሉ እና እርጥብ ቀጤማ በመያዝ በየመንደሩ እየዞሩ ‹‹በመስቀሉ ሰላምን አደረገ፤ትንሣኤውንም ገለጠልን›› በማለት ቀጤማውን ለምእመናን ያድላሉ:: ምእመናንም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ስጦታ ለካህናቱ ሰጥተው ቀጤማውን  ተቀብለው በራሳቸው ላይ ያስራሉ::

ልጆች! ከዚህም በተጨማሪ የሕማማት ሳምንት ዕለታት የየራሳቸው ስያሜና ታሪክ  አሉአቸው::

ሰኞ - ‹የቤተ መቅደስ መንጻት ቀን›› ይባላል:: ጌታች መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመቅደሱ ውስጥ እና ዙሪያውን ይሸጡ ይለውጡ የነበሩ ነጋዴዎችን ገርፎ ከቤተ መቅደስ ያስወጣበት እና ቤተ መቅደሱን ያነጻበት ቀን ነው::

ማክሰኞ -  ‹‹የጥያቄና መልስ ቀን›› በመባል ይታወቃል:: ጌታችን ሰኞ ባደረገው ነገር ላይ(ሻጮችና ለዋጮችን ለምን ገርፎ እንዳስወጣ) አይሁድ ጥያቄ የጠየቁበትና እርሱም መልስ የሰጠበት ቀን ነው::

ረቡዕ - ‹‹የምክር ቀን›› ይባላል:: የአይሁድ ካህናትና ጸሐፍት ጌታን እንዴት መያዝ እንደሚችሉ የመከሩበት ቀን ነው:: ‹‹የመልካም መዓዛ ቀን›› እና ‹‹ የለቅሶ ቀን›› በመባልም ይታወቃል::

ሐሙስ - ‹‹ጸሎተ ሐሙስ›› በመባል ይታወቃል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁድ ሊይዙት እስኪመጡ ድረስ በጌቴሴማኒ የአትክልት ሥፍራ ሲጸልይ የነበረበት ቀን ስለሆነ ነው:: ጌታችን ዝቅ ብሎ የደቀ መዛሙርቱንም እግር ያጠበበት ቀን ስለሆነ ‹‹ሕጽበተ እግር›› በመባልም ይጠራል:: ጌታችን ምሥጢረ ቁርባንን የጀመረበት ቀን በመሆኑም ‹‹የምሥጢር ቀን›› በመባል ይጠራል::

ዓርብ - ይህ ቀን አይሁድ በክፋት እና በምቀኝነት ተነሳስተው ጌታን የሰቀሉበት ቀን በመሆኑ ‹‹ዕለተ ስቅለት›› ይባላል:: ይህ ቀን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ዘር በሙሉ ለማዳን በመስቀል ላይ የተሰቀለበት ታላቅ ቀን ነው::

ቅዳሜ - ‹‹ ቀዳም ሥዑር›› በመባል ይታወቃል:: በዚህ ቀን ጌታችን በመቃብር አርፎ የዋለባት ቀን በመሆኑ ይጾማል:: ቀዳም ሥዑር የተባለበትም በዓመት አንድ ቀን ስለምትጾም ነው::

ልጆች! በሰሙነ ሕማማት ክርስቲያኖች ሁሉ የጌታችንን ውለታ እያሰቡ የሚጸልዩበት፣ የሚያዝኑበት ፣የሚሰግዱበት ከሌሎች ቀናት የተለዩ ቀናት ናቸው:: እናንተም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳችሁ እንድትጸልዩ፣ እንድትሰግዱ እንነግራችኋለን እሺ ልጆች!

*መዋዕለ ጾሙን አስፈጽሞ ለብርሃነ ትንሣኤው*

*በሰላም ያድርሰን ያድርሳችሁ!*

# የቅዱሳት ሥዕላት ክብር ከየት ወደ የት?

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ቅዱሳት ሥዕላት በኢትጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ቦታ አላቸው። የሥላሴዎች፣ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢሱስ ክርስቶስ፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ የቅዱሳን መላእክት፣ የቅዱሳን ሰማዕታት ሥነ ሥዕል መሣል ብሎም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማድረግ እና ለጸሎት እና ለትምህርት መጠቀም የተለመደ ነው። አብያተ ክርስቲያናቱንም ሆነ ገዳማቱን ካለ ቅዱሳት ሥዕላት ማሰብ አስቸጋሪ ነው። ብዙዎቻችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ በቅዱሳት ሥዕላቱ ፊት በመቆም፣ በመንበርከክ እንዲሁም በመስገድ ጸሎት እናደርሳለን፣ ሰላምታ እናቀርባለን ፣ ምልጃ እንጠይቃለን። በቤታችንም ለቅዱሳት ሥዕላት የተለየ ቦታ አዘጋጅተን በክብር በማስቀመጥ ለጸሎት አገልግሎት እንጠቀምባቸዋለን።

ቅዱሳት ሥዕላት በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በቤታችን ለጸሎት የምንጠቀመው ዝም ብለን ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የትመጣውን አብነት አድርገን ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ነቢዩ ሙሴን የኪሩብን ሥዕል በሥርየት መከደኛው ላይ እንዲያዘጋጅ፣ በዚያም ላይ ተገልጦ እንደሚያነጋግረው ነግሮታል (ዘጸ ፳፭፥፲፰–፳፪።) በሐዲስ ኪዳንም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ‹‹ምስለ ፍቁር ወልዳ ›› ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ሥሏታል። ቅዱስ ኤፍሬም በእሑድ ውዳሴ ማርያም ላይ ‹‹በእግዚአብሔር ሥዕል የተሣሉ ኪሩቤል የሚጋርዱሽ መቅደስ አንቺ ነሽ›› በማለት በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር አዛዥነት በሙሴ ሠሪነት የተከናወነውን የሥነ ሥዕል ምንነት ያጠናክርልናል።

እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የትመጣ ያላቸው የአምልኮ መግለጫ፣ ነገረ ድኅነትንም ሆነ ነገረ ቅዱሳንን የምንማርባቸው ቅዱሳት ሥዕላት ቤተ ክርስቲያን ከሰጠቻቸው የክብር ቦታ ወርደው ለጸሎት፣ ለአምልኮ፣ ለትምህርት መዋላቸው ከቁብ ሳይቆጠር እንደ አልባሌ እና ተራ ነገር ማየት የተለመደ ሆኗል። በቤተ ክርስቲያን ሳይቀር በቅጽረ ግቢው አንዳንድ ቦታ ላይ ተጥለው፣ ተቀዳደው የሚታዩበት ጊዜ ጥቂት አይደለም። እዚያ ቤተ መቅደስ ውስጥ የምንሳለምውን፣ የምንሰግድለትን፣ ሥዕለ ቅዱሳን ውጪ ላይ ሲረገጥ ማየት በአእምሮ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም።

ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ብዙም ሳንርቅ በጎዳና ላይ እንዳልባሌ ዕቃ ተሰጥተው የምናያቸው ቅዱሳት ሥዕላት ቁጥር ቀላል አይደሉም። ከሌሎች ተራና ዓለማዊ ሸቀጣ ሸቀጦች ጋር ተደባልቀው ፀሐይና ብርድ እየተፈራረቀባቸው አቧራ እየጠጡ መንገድ ላይ የሚሸጡት ቅዱሳት ሥዕላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ክብር ሰጥታ ለአምልኮ የምትጠቀምባቸው የአምልኮ መገለጫዎቿ መሆናቸውን ስንቶቻችን እንገነዘብ ይሆን? ምእመኑም እንደ ተራ እቃ ከመንገድ ላይ እየገዛ ሲጠቀምባቸው እውነት ያላቸውን ክብር እያሰበ ነው ወይ? ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም በክብር ያልተያዙ ቅዱሳት ሥዕላቱን እንዴትስ አክብሮ ሊጸልይባቸው፣ ሊሰግድላቸው ይችላል? ነገሩ ዘልማድ ነው የሚመስለው።

ወደ ቤትም ከደረሱ በኋላ በእያንዳንዱ ምእመናን ቤት የሚኖራቸው የክብር ሥፍራ ሌላው አስተዛዛቢ ጉዳይ ነው። ቅዱሳት ሥዕላቱ አንዳንዱ ቤት እንደማንኛውም ዓለማዊ ሥዕል ቦታ ሳይመረጥላቸው ይሰቀላሉ ፣ የጸሎት ሳይሆን የቤት ማድመቂያም ነው የሚመስሉት። ከተሣሉበት ዓላማ ጋር የማይገናኝ አገልግሎትም ነው ያላቸው። ዛሬ ዛሬ ቤት ውስጥ እንዳልባሌ ከመሰቀላቸው አልፎ በየ ቡና ቤቱ እና በየመጠጥ ቤቱ ቅዱሳት ሥዕላትን ማየት የተለመደ ሆኗል። ይህም የእያንዳንዱን ምእመን ለቅዱሳት ሥዕላት ያለውን የዕውቀት ደረጃ አናሳ መሆን የሚያሳይ ነው።

በኪስ እና በቦርሳ የሚያዙ ቅዱሳት ሥዕላት ዕጣ ፈንታም ከላይ ካነሣናቸው ገጠመኞች የተለየ አይደለም። በኪስም ሆነ በቦርሳ እንደ ተራ ነገር ከብር፣ ከተለያዩ ወረቀቶች፣

ከሴቶች የተለያዩ የመዋቢያ ዕቃዎች ጋር ተደባልቀው የሚያዙ ቅዱሳት ሥዕላት የተሣሉበትን ዓላማ ከመግለጽ ይልቅ የኪስ ወይም የቦርሳ ማድመቂያ ነው የሚመስሉት፡፡ በቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀምጠው፣ ተሰቅለው በፍርሃት የምንሳለማቸው ቅዱሳት ሥዕላት ከተራ ወረቀት ጋር ከቦርሳና ከኪስ ተመዘው ሲወጡ እንደ ማየት የሚያሳዝን ብሎም የሚያስተዛዝብ ነገር የለም፡፡

**ከሌሎች ተራና ዓለማዊ ሸቀጣ ሸቀጦች ጋር ተደባልቀው ፀሐይና ብርድ እየተፈራረቀባቸው አቧራ እየጠጡ መንገድ ላይ የሚሸጡት ቅዱሳት ሥዕላት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ክብር ሰጥታ ለአምልኮ የምትጠቀምባቸው የአምልኮ መገለጫዎቿ መሆናቸውን ስንቶቻችን እንገነዘብ ይሆን? ምእመኑም እንደ ተራ እቃ ከመንገድ ላይ እየገዛ ሲጠቀምባቸው እውነት ያላቸውን ክብር እያሰበ ነው ወይ? ለማለት ያስቸግራል፡፡**

በቤተ ክርስቲያን ካላቸው ክብር አንሰው ከመገኘታቸውም በላይ የቅዱሳት ሥዕላቱ አሣሣል የተሣሉበትን ዓላማ የዘነጋ ነው፡፡ ቅዱሳት ሥዕላት በቤተ ክርስቲያን ሲሳሉ የራሳቸው ሕግ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥርዓት አላቸው፡፡ ሥዕላቱ ምሥጢረ ሥላሴን፣ ምሥጢረ ሥጋዌን፣ ምሥጢረ ትንሣኤን፣ ነገረ ድኅነትን፣ ነገረ ቅዱሳንን በትክክል እንዲያሳዩ ሆነው ነው የሚሣሉት፡፡ የሚሳሉበት የቀለም ዓይነት ሳይቀር የተወሰኑ፣ ታሪካዊና መንፈሳዊ ትርጓሜ ያላቸው ናቸው፡፡

ዛሬ ዛሬ በገበያ ላይ የምናገኛቸው አንዳንድ ሥዕላት ግን ከታሪክም ሆነ ከዶግማ የተፋቱ ሆነው ነው የሚታዩት፡፡ እነዚህ ሥዕላት በገበያ ብቻ የተወሰኑ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት ላይ ሳይቀር የሚሸጡ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ የትንሣኤ ሥዕል እንወሰድ በብዙ መልኩ ተሥሎ የምናገኘው በየቤታችንም አድርገን የምንጠቀምበት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ‹‹መቃብር ተከፍቶ ጌታችን መቃብር ውስጥ ቆሞ የሚያሳይ ነው፡፡›› መጽሐፍ ቅዱስ ጌታችን ‹‹መቃብር ክፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል›› ከሙታን ተለይቶ እንደተነሳ ነው የሚነግረን (ማቴ፳፰፥፩–፯፡፡) ይህ ሥዕል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳይቀር ተሥሎ እያየን ነው፡፡ ሌሎችም ቅዱሳት ሥዕላት በተመሳሳይ ከታሪካቸው ከእውነተኛው ገጽታቸው ጋር የተጣረሱ ናቸው፡፡

እነዚህ ሁሉ በቅዱሳት ሥዕላት ዙሪያ ከምናያቸው ችግሮች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የሚገርመው ዛሬም ድረስ የሚገዛውም ሆነ የሚጠቀምበት የቤተ ክርስቲያን ልጅ በቤተ ክርስቲያን ያላቸውን አስተምህሮም ሆነ ክብር በማገናዘብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በአንድም በሌላ ችግሮቹ በሁላችንም ዘንድ ይታያሉና፡፡ ሆኖም ችግሩን ብቻ ሳይሆን ችግሩን እንዴት እናስወግድ ማለት ከእኛ ይጠበቃል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ቅደስት ቤተ ክርስቲያን እንደሌሎቹ ትምህርቶች ሁሉ ስለ ቅዱሳት ሥዕላት ክብር እንዲሁም በቤትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደምንገለገልባቸው ትምህርት ልትሰጥ ይገባል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ጠብቀው የተሳሉ ቅዱሳት ሥዕላት የትኞቹ መሆናቸውን እንዲሁም ከሌሎቹ በምን እንደሚለዩ ማሳየት ይጠበቅባታል፡፡

ቅዱሳት ሥዕላቱን ገዝተን ለቤተ ክርስቲያን የምንሰጥም ሆነ በቤታችን የምንጠቀም ክርስቲያኖች ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያን ሥዕል መግዛት ይገባናል፤ እንዲሁም ቅዱሳት ሥዕላቱን በክብር ልንይዝ ይጠበቅብናል፡፡

# ‹‹ከሌላ ሴት ብወልድ ኃጢአት ይሆንብኝ ይሆን?››

ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች! እንደምን ሰነበታችሁ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ድኅና ነኝ። ስሜ ገብረ ትንሣኤ ይባላል የ፴፰ ዓመት ጎልማሳ ነኝ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ፈተና የሆነብኝን ነገር ላካፍችሁ ወደ እናንተ ጻፍኩ። ነገሩ እንዲህ ነው እኔ እና ባለቤቴ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ቊርባን ከተጋባን ዐሥር ዓመት ሆነን ነገር ግን ቤታችን በልጅ አልተባረከም። የሞላ ሀብት ቢኖረንም እስከዛሬ ድረስ ልጅን መውለድ አልቻልንም። የመጀመሪያዎቹን ሦስት ዓመታት እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ጠበቅን ምንም ነገር የለም።

በመሀል እኔ እንድንመረመር ለባለቤቴ ጥያቄ አቀረብኩና ወደ ሆስፒታል ሄድን ስንመረመር እኔ መውለድ እችላለሁ እርሷ መውለድ አትችልም(መሀን ናት)። ይህ ውጤት ግን ለቤታችን ሰላምን ይዞ አልመጣም በመሀከላችን የነበረው ፍቅር እየቀዘቀዘ ከመሄዱም በላይ ዘወትር በረባ ባረባው መጨቃጨቅ ሥራችን ሆነ። ለዚህ ደግሞ ትልቁን ድርሻ የምትወስደው የትዳር አጋሬ ናት። በሆነ ባልሆነው ይከፋታል ሲያሻት ታኮርፈኛለች። በስሕተት ስለ ወለዱ ሰዎች ካወራሁ ወይም ከጓደኞቼ ጋር አምሽቼ ከገባሁ ‹‹እኔ መውለድ ስለማልችል ጠልተኸኝ ነው፤ የምትወልድ ማግባት ትችላለህ ›› እያለች ወደ ውጪ እንዳይ ትገፋኛለች። እኔ መፋታት ኃጢአት ነው ብዬ አስባለሁ ፤ነገር ግን በየዕለቱ በዚህ ምክንያት ቤቴ መግባት እስኪያስጠላኝ ደርሻለሁ።

እኔም ልጅ እንዲኖረኝ በብርቱ እጓጓለሁ ዘር ተክቼ ባልፍ ንብረቴን የሚወርስ ልጅ ቢኖረኝ ደስ ይለኛል። ከሌላ ወልጄ አምጥቼ አብረን ብናሳድግ ብዬ አስባለሁ ነገር ግን ይህንን ለባለቤቴ መንገር እፈራለሁ። አንዳንዴ በድብቅ ባደርገውስ ባወቀች ጊዜ ትወቅ የሚል ሐሳብ ይመጣብኛል። ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች በእነዚህ ሁለት ሐሳቦች ውስጥ ወድቄአለሁና ምን ትመክሩኛላችሁ? ‹‹ከሌላ ሴት ብወልድ ኃጢአት ይሆንብኝ ይሆን?››

ውድ ወንድማችን ገብረ ትንሣኤ በቅድሚያ ችግርህን (ምሥጢርህን) ስላካፈልከን እናመሰግናለን፤ እንዲህ ዓይነት ገጠመኞች በብዙ ሰዎች ሕይወት ውስጥ በወንዶችም በሴቶችም ላይ ይከሠታሉና የአንተ የሕይወት አጋጣሚ በእንዲህ ዓይነት ሕይወት ውስጥ ላሉ ሁሉ ሊጠቅም ስለሚችል እና አስተማሪ በመሆኑ ለዚህ ዝግጅት እንዲስማማ አድርገን አቅርበነዋል፤ መልካም ንባብ።

ውድ ወንድማችን አንተን የገጠመህ ችግር የባለቤትህ (የትዳር አጋርህ) መሀን መሆን ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ በቤታችሁ ውስጥ ሰላም የማጣታችሁ ጉዳይ ነው። ይህ በቤትህ ውስጥ መፈጠሩ ደግሞ ልብህ ‹‹ከሌላ ሴት ልጅ ወልጄ ላምጣ›› ወደሚለው ሐሳብ እያዘነበለብህ ነው። በተለይ የባለቤትህ ጠባይ ከዕለት ወደ ዕለት እየተለወጠ መምጣቱ እና በሆነ ባልሆነው አኩራፊ መሆንዋን ልትረዳት ይገባል። አንተው እንደገለጽክልን እንዲህ ዓይነት ጠባይ ያመጣችው መሀን መሆንዋን ካወቀች በኋላ ነውና እንደ አንድ የትዳር አጋር ልትንከባከባት እና የምትናገረውንም ልታልፋት ይገባል። የነቢዩ ሳሙኤል እናት ሐና ሳሙኤልን እስክትወልድ ድረስ በጣውንቷ ትቀናባትና ታዝን ነበር ከዚያም አልፎ ትበሳጭ፣ ምግብ አልበላም

በማለትታለቅስም ነበረ በዚህ ጊዜ ባለቤትዋ ሕልቃና ግን እንዳታለቅስ እንዳታዝን ምግብም እንድትበላ ይመክራት ነበር (፩ኛ ሳሙ ፩ ፥ ፩–፰፡፡) አንተም ስሜትዋ የተጎዳ ባለቤትህን ልታዝንላት ልትንከባከባት እና ልትመክራት ይገባል እንጂ ልትበሳጭባት አይገባም፡፡

በትዳር እያለህም ከሌላ ሴት ልጅ ወልዶ ማምጣትም ከላይ በዝርዝር ለማስቀመጥ እንደሞከርነው ኃጢአት ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ከጋብቻ ውጪ የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግኑኝነት እጅግ ኃጢአት ነው፡፡ አንተም ከተከበረው ትዳርህ ውጪ የምታደርገው ግኑኝነት ፍጹም ኃጢአት ነውና ወደዚያ ልታስብ አይገባም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ ከዝሙት ራቁ ፤ ኃጢአት የሚሠራ ሰው ሁሉ ከሥጋው ውጪ ይሠራልና፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን ራሱ በሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል፡፡›› (፩ኛ ቆሮ ፮፥፲፰) ይላልና አንተም ከባለቤትህ ተለይተህ በዝሙት ኃጢአት መውደቅ አይገባህም፡፡ ‹‹ሴሰኞች በእግዚብሔር መንግሥት ርእስት እንደሌላቸው ይህንን ዕወቁ›› (ኤፌ.፭፥፭) ተብሎ የተጻፈውን ልታስተውል ይገባል፡፡ ሴሰኝነት አመንዝራነት ማለት ደግሞ በከበረ ትዳር ላይ ሄዶ ማመንዘር ነው፡፡ ሐዋርያው እንደነዚህ ያሉትን ነው አመንዝሮች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም በማለት የሚያስጠነቅቃቸው፡፡

ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹ከሴት ጋር የሚያመነዝር ግን አእምሮ የጎደለው ነው፡፡ እንዲህም የሚያደርግ ነፍሱን ያጠፋል›› ይላል ምሳ. ፮፥፴፪ ፩ኛቆ ፯፥፴፮ በመሆኑም በልጅ ፍለጋ ሰበብ ከትዳርህ ውጪ የምታደርገው የግብረ ሥጋ ግኙኝነት ለሥጋ ብቻ የሚተርፍ ሳይሆን ነፍስንም የሚያጠፋ ነው፡፡ በመሆኑም ከእንደዚህ ዓይነት ነፍስን እስከማጣት ከሚያደርስ ኃጢአት ልትሸሽ ልትርቅ ይገባል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ‹‹በዋጋ ተገዝታችኋልና የራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ›› ፩ኛቆሮ. ፯፥፴፮ እንዳለ ከእግዚአብሔር የተሰጠህን ቅዱስ ሥጋ ለጊዜያዊ ምኞትህ የልብህን መሻት ለመፈጸም ብለህ በፍጹም ሥጋህን ማርከስ አይገባህም፡፡ ምክንያቱም አንተ የአንተ ሳትሆን የፈጣሪህ የክርስቶስ አካል ነህና፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ፆርም አንተን ከእግዚአብሔር ሊለይህ የመጣ ፈተና ነውና ከእንደዚህ ዓይነቱ የኃጢአት ምኞት በጊዜ ልትርቅ ይገባል፡፡

**ውድ ወንድማችን ከትዳር አጋርህ ጋር ሆነህ ከዚህ ይልቅ በተስፋ በመጠበቅ በጸሎት በምልጃ ብትጸኑ አንድ ቀን እግዚአብሔር ለጸሎታችሁ መልስ ይሰጣችኋል፡፡ ቅድስት ሐና የሳሙኤል እናት ለረጅም ጊዜ ልጅ አልነበራትም በዚህ ምክንያት ሁል ጊዜ ታዝን ትተክዝ ነበረ፡፡ አብዝታ ወደ እግዚአብሔር በመጮኋ እግዚአብሔር አምላክ ለጸሎትዋ ለልቅሶዋ መልስ ሰጣት የእግዚአብሔርን ቤት የሚያገለግል የእስራኤልን ነገሥታት የሚቀባ ታላቁን ነቢይ ሳሙኤልን ሰጣት (፩ኛሳሙ.፩፥፩—፳፰)**

ውድ ወንድማችን ከትዳር አጋርህ ጋር ሆነህ ከዚህ ይልቅ በተስፋ በመጠበቅ በጸሎት በምልጃ ብትጸኑ አንድ ቀን እግዚአብሔር ለጸሎታችሁ መልስ ይሰጣችኋል፡፡ ቅድስት ሐና የሳሙኤል እናት ለረጅም ጊዜ ልጅ አልነበራትም በዚህ ምክንያት ሁል ጊዜ ታዝን ትተክዝ ነበረ፡፡ አብዝታ ወደ እግዚአብሔር በመጮኋ እግዚአብሔር አምላክ ለጸሎትዋ ለልቅሶዋ መልስ ሰጣት የእግዚአብሔርን ቤት የሚያገለግል የእስራኤልን ነገሥታት የሚቀባ ታላቁን ነቢይ ሳሙኤልን ሰጣት (፩ኛሳሙ.፩፥፩–፳፰)

ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚያስተምረን አብርሃም እና ሣራም ልጅ አልነበራቸውም ፤ሁለቱም ፈጽመው ባረጁበት ሰዓት ሣራም የሴት ወግ ማየት ባቆመችበት የእርጅና ዘመን እግዚአብሔር ይስሐቅን ሰጣቸው፡፡ (ዘፍ. ፲፰፥፱–፲፭) ይስሐቅን መስጠት ብቻ ሳይሆን ለሣራ አሕዛብና የአሕዛብ ነገሥታት ከእርስዋ እንደሚወጡ ነግሯታል፡፡ (ዘፍ.፲፯፥፲፯) በአዲስ ኪዳንም በተመሳሳይ ካህኑ ዘካርያስና ሚስቱ ኤልሳቤጥ ልጅ አልነበራቸውም ካህኑ ዘካርያስ በቤተ መቅደስ እያጠነ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ ልጅ እንደሚወልድ ሲነግረው ሁለቱም አርጅተው ስለነበረ የመልአኩን ቃል አላመነም ፤ነገር ግን መልአኩን ስላላመነ ዲዳ ከሆነ በኋላ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን ሲወለድ አንደበቱ እንደተፈታለት እናያለን፡፡ (ሉቃ. ፩፥፭–፳፭)

ውድ ወንድማችን እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ በጸሎት እየተጋህ በቤቱ ልትኖር ይገባል፡፡ ‹‹ ጌታ ቅርብ ነው፡፡ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ›› እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ (ፊል. ፬፥፮-፯) አንተም ከዚህ በኋላ ሚስቴ ልጅ ልትወልድ አትችልም በሚል ስጋት ውስጥ ገብተህ ሐሳብህን በሁለት መክፈል የለብህም፡፡ ይልቁንም ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር አሳልፈህ በመስጠት ከእርሱ የሚመጣውን በረከት ብትጠብቅ መልካም ነው፡፡ አምላካችን እግዚዘብሔር የታመነ አምላክ ነውና የልብ መሻታችንን እና ጩኸታችንን ሰምቶ ፈቃዳችንን ለመፈጸም የሚሳነው ነገር የለም፡፡ ይህ ይፈጸም ዘንድ ከአንተና ከባለቤትህ የሚጠበቀው ፍጹም እምነት ነው፡፡

ስለዚህ ውድ ወንድማችን ገብረ ትንሣኤ ‹‹ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና›› ሉቃ. ፩፥፴፯ አንተ እና የትዳር አጋርህ የልባችሁን ሥጋት እና ጥርጣሬ ከውስጣችሁ አስወግዳችሁ ልባችሁን በእግዚአብሔር ላይ በማድረግ እርሱን በተስፋ ልትጠብቁት ይገባል፡፡ ከጸሎታችሁም ባሻገር እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ በእርጅና ዘመናቸው ሁሉ ሲጠብቁት በስተመጨረሻ በልጅ የባረካቸውን እነዚህን ቅዱሳን የእግዚአብሔር ሰዎች አብነት ማድረግ ይኖርባችኋል፡፡ በእግዚአብሔር ፊትም በመንበርከክ በጸሎት፣ በምልጃ ልትማጸኑት ይገባል፡፡ አብርሃምና ሣራን፣ ሕልቃናንና ሐናን እንዲሁም ካህኑ ዘካርያስንና ኤልሳቤጥን፣ ጺጋ ዘአብንና እግዚእ ኃሪያን ያሰበ አምላክ እናንተንም ያስባችኋል ፤ በልጅም በረከት ይባርካችኋል፡፡ አስቀድመን እንደተናገርነው ከእናንተ የሚጠበቀው በእምነት ወደ እግዚአብሔር ቀርባችሁ በፍጹም ልብ መለመን ብቻ ነው፡፡ መጽሐፍ ‹‹ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና›› (ሉቃ. ፩፥፴፯) እንዳለ የልባችሁን መሻት ይሰጣችኋል፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ጸሎታችሁን ሰምቶ የልባችሁን መሻት ይሰጣችሁ ዘንድ መልካም ፈቃዱ ይሁን፡፡